# ምዕራፍ 1




# እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች

## 1.1 በመቶዎች መቁጠር

### ትግበራ 1.1

ሀ. እስከ 100 ያሉትን የ10 ብዜቶች ዘርዝር/ሪ፡፡

ለ.የ100 ብዜቶችን ቁጠር/ሪ፡፡

ሐ.200፣ 300፣ 400፣ 500፣ 600 እና 700ን ክፍል ውስጥ አንብብ/ቢ፡፡

መ.እንደ 400፣ 500፣ 600እና 700 ያሉ ቁጥሮችን በ100 ብዜቶች ድምር ግለጽ/ ጪ፡፡.

**ምሳሌ 1**

ሀ. $2 \times 10 =$ ______ ለ. $3 \times 10 =$ ______

ሐ. $2 \times 100 =$ ______ መ. $3 \times 100 =$ ______

**መፍትሔ**

| | |
|---|---|
| ሀ. $10 + 10 = 20$ ይሆናል፡፡<br>$2 \times 10 = 10 + 10 = 20$<br>ስለዚህ 20 የ10 ብዜት ነው፡፡ | ለ.$10 + 10 + 10 = 30$ ይሆናል፡፡<br>$3 \times 10 = 10 + 10 + 10 = 30$<br>ስለዚህ 30 የ10 ብዜት ነው፡፡ |

| | |
|---|---|
| ሐ. 100 + 100 = 200 ይሆናል። | መ. 100 + 100 + 100 = 300 ይሆናል። |
| 2 × 100 = 100 + 100 = 200 | 3 × 100 = 100 + 100 + 100 = 300 |
| ስለዚህ 200 የ100 ብዜት ነው። | ስለዚህ 300 የ100 ብዜት ነው። |

## ምሳሌ 2

ከዚህ በታች የተሰጡትን የ 100 ብዜቶችን በሌላ 100 ብዜቶች ድምር ጻፍ/ፊ።

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. 200 = 100 + ______ | ለ. 400 = 200 + ______ | ሐ. 600 = 400 + ______ |
| መ. 700 = 500 + ______ | ሠ. 800 = 700 + _____ | ረ. 500 = 300 + ______ |

## መፍትሔ

ሀ. 200 = 100 + _______

200 በ100 ብዜቶች ድምር ሊፃፍ ይችላል።

ይህም 200 = 100 + 100 ይሆናል።

ለ. 400 = 200 + ______

400 በ100 ብዜቶች ድምር ሊፃፍ ይችላል።

ይህም 400 = 200 + 200 ይሆናል።

ሐ. 600 = 400 + _______

600 በ100 ብዜቶች ድምር ሊፃፍ ይችላል።

ይህም 600 = 400 + 200 ይሆናል።

መ. 700 = 500 + 200     ሠ. 800 = 700 + 100     ረ. 500 = 300 + 200

## መልመጃ 1.1

1. የ100 ብዜቶችን ባዶ ቦታ ላይ ሙላ/ዪ።

| × | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 100 | | 200 | | | | 600 | | | 900 | 1000 |

**2.** ከዚህ በታች በአሀዝ የተጻፉትን ቁጥሮች በፊደል ጻፍ/ፊ።

| ተ.ቁ. | ቁጥር | በፊደል |
|---|---|---|
| ሀ | 100 | |
| ለ | 200 | |
| ሐ | 300 | |
| መ | 400 | አራት መቶ |
| ሠ | 500 | |
| ረ | 600 | |
| ሰ | 700 | ሰባት መቶ |
| ሸ | 800 | |
| ቀ | 900 | |
| በ | 1000 | አንድ ሺህ |

**3.** የሚከተሉትን በ100 ብዜቶች ድምር ጻፍ/ፊ።

ሀ. 300 = 100 +______ ለ. 500 = 200 + ______ ሐ. 800 = 400 + ______

መ. 900 = 600 + ______ ሠ. 1000 = 700 + _____ ረ. 700 = ____ + 100

ሰ. 200 + _____ = 500 ሸ. 900 = 100 + ______ ቀ. 800 = ____ + 300

**4.** አያንቱ ከእናቷ 400ብር እና ከአባቷ ደግሞ 500ብር ተቀበለች። በአጠቃላይ ስንት ብር ተቀበለች?

# 1.2 እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች

## ትግበራ 1.2

**1.** የጨሌዎቹ ብዛት ስንት ነው?



**2.** ከዚህ በታች የተሰጡትን ቁጥሮች ድምጻችሁን ከፍ በማድረግ ክፍል ውስጥ አንብቡ።

ሀ. 120 ለ. 254 ሐ. 753 መ. 871 ሠ. 917

## ምሳሌ 3

የሚከተሉትን ቁጥሮች በማንበብ በፊደል ጻፍ/ፊ፡፡

ሀ. 528 ለ. 976 ሐ.802 መ. 754

### መፍትሔ

ሀ. 528 = አምስት መቶ ሃያ ስምንት፡፡

ለ. 976 = ዘጠኝ መቶ ሰባ ስድስት፡፡

ሐ. 802 = ስምንት መቶ ሁለት፡፡

መ. 754 = ሰባት መቶ ሃምሳ አራት፡፡

## ምሳሌ 4

የሚከተሉትን በፊደል የተጻፉትን ቁጥሮች በአኃዝ ጻፍ/ፊ፡፡

ሀ. አራት መቶ ሰባ ስምንት፡፡ ለ. ስምንት መቶ ዘጠና ሁለት፡፡

ሐ. ዘጠኝ መቶ ሰላሳ ሶስት፡፡ መ. አንድ መቶ ስልሳ አንድ፡፡

ሠ. ሶስት መቶ ሰባ ዘጠኝ፡፡

### መልስ

ሀ. አራት መቶ ሰባ ስምንት = 478 ለ. ስምንት መቶ ዘጠና ሁለት = 892

ሐ. ዘጠኝ መቶ ሰላሳ ሶስት = 933 መ. አንድ መቶ ስልሳ አንድ = 161

ሠ. ሶስት መቶ ሰባ ዘጠኝ= 379

## መልመጃ 1.2

1. የሚከተሉትን በአኃዝ የተጻፉትን ቁጥሮች በፊደል ጻፍ/ፊ፡፡

ሀ. 285 ለ. 309 ሐ. 457 መ.794

ሠ. 673 ረ. 801 ሰ. 529 ሸ. 980

2. የሚከተሉትን በፊደል የተጻፉትን ቁጥሮች በአኃዝ ጻፍ/ፊ፡፡

ሀ. አራት መቶ ሃምሳ ስድስት = __________

ለ. ሁለት መቶ ሰላሳ ሰባት = __________

ሐ. አንድ መቶ ዘጠና አንድ = __________

መ. ስምንት መቶ ሰማንያ አምስት = __________

ሠ. ሰባት መቶ አምስት = __________

## ምሳሌ 5

ከዚህ በታች የተሰጡትን ቁጥሮች መነሻ በማድረግ ወደ ፊትና ወደኃላ ቁጠር/ሪ፡፡

ሀ. 150 ለ. 512 ሐ. 408

### መፍትሔ

ሀ. 150

ወደ ፊት ስንቆጥር 150፣ 151፣ 152፣ 153፣ 154፣… ፣1000

ወደ ኃላ ስንቆጥር 150፣ 149፣ 148፣ 147፣… ፣1

ለ. 512

ወደ ፊት ስንቆጥር 512፣ 513፣ 514፣ 515፣ 516፣… ፣1000

ወደ ኃላ ስንቆጥር 512፣ 511፣ 510 ፣509፣ 508፣…፣ 1

ሐ. 408

ወደ ፊት ስንቆጥር 408፣ 409፣ 410፣ 411፣ 412፣…፣ 1000

ወደ ኃላ ስንቆጥር 408፣ 407፣ 406፣ 405፣ 404፣ 403፣…፣ 1

## ምሳሌ 6

ከዚህ በታች የተሰጡትን የተሸከርካሪ ሰሌዳ ቁጥር አንብብ/ቢ፡፡

ሀ

ለ




## መፍትሔ

ሀ. ዜሮ ስድስት ሁለት ሶስት ስምንት ተብሎ ይነበባል፡፡

ለ. ዜሮ ሁለት ሁለት ስድስት ሰባት ተብሎ ይነበባል፡፡

## መልመጃ 1.3

1. ከዚህ በታች ከተሰጡት ቁጥሮች በመነሳት አንድ አንድ በመዝለል ወደ ፊት በመቁጠር እስከ 1000 ጻፍ/ፊ፡፡

ሀ. 420 ለ. 643 ሐ. 892 መ. 108

2. ከዚህ በታች ከተሰጡት ቁጥሮች በመነሳት ሁለት ሁለት በመዝለል ወደ ኃላ እስከ 100 በመቁጠር ጻፍ/ፊ፡፡

ሀ. 180 ለ. 205 ሐ. 431 መ. 518

3. ከዚህ በታች ከተሰጡት ቁጥሮች በመነሳት ሶስት ሶስት በመዝለል ወደ ፊት በመቁጠር እስከ 1000 ጻፍ/ፊ፡፡

ሀ. 100 ለ. 235 ሐ. 430 መ. 715

4. ከዚህ በታች የተሰጠውን የተሽከርካሪ የሰሌዳ ቁጥር በማንበብ በፊደል ጻፍ/ፊ፡፡



# 1.3 እሰከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች የቁጥር ቤት ዋጋ

## ሀ. የቁጥር ቤትን ማንበብና በሠንጠረዥ ማስቀመጥ

### ትግበራ 1.3

1. በ875 ውስጥ የ8፣ 7 እና 5 የቁጥር ቤት ዋጋ ስንት እንደሆነ በቡድን ተወያዩበት፡፡
2. በ906 ውስጥ የ9፣ 0 እና 6 የቁጥር ቤት ዋጋ ስንት እንደሆነ በቡድን ተወያዩበት፡፡

### ምሳሌ 7

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 100 | 100 | 100 | 10 | 10 | 1 | 1 | 1 | 1 |

ሀ. ስንት መቶዎች አሉ?

ለ. ስንት አስሮች አሉ?

ሐ. ስንት አንዶች አሉ?

መ. አንድ ላይ በአኃዝ ጻፍ/ፊ፡፡

**መፍትሔ**

ሀ. ሶስት መቶዎች አሉ፡፡
ይህም ሲጻፍ 300 ይሆናል፡፡

ለ. ሁለት አስሮች አሉ፡፡
ይህም ሲጻፍ 20 ይሆናል፡፡

ሐ. አራት አንዶች አሉ፡፡
ይህም ሲጻፍ 4 ይሆናል፡፡

መ. አንድ ላይ በአኃዝ 324 ይሆናል፡፡

### ምሳሌ 8

ከዚህ በታች የተሰጡትን ቁጥሮች ሠንጠረዥ በመጠቀም የቁጥር ቤታቸውን ግለጽ/ጪ፡፡

ሀ. 456

ለ. 938

**መፍትሔ**

ሀ. 456




**ለ.** 938




## አስተውል/ዪ

የቁጥርን የቁጥር ቤት ስናነብ በመጀመሪያ የአንድን ቤት ቀጥሎ የአስርን ቤት በመጨረሻ የመቶ ቤትን እናነባለን፡፡

## ምሳሌ 9

ከዚህ በታች ለተሰጡት ቁጥሮች የመቶን ቤት፣የአስርን ቤት እና የአንድን ቤት አንብቡ፡፡

**ሀ.** 200　　**ለ.** 700　　**ሐ.** 758

**መፍትሔ**

| | ቁጥር | መቶዎች | አስሮች | አንዶች |
|---|---|---|---|---|
| ሀ. | 200 | 2 | 0 | 0 |
| | ሁለት መቶ | | | |
| ለ. | 700 | 7 | 0 | 0 |
| | ሰባት መቶ | | | |
| ሐ. | 758 | 7 | 5 | 8 |
| | ሰባት መቶ ሃምሳ ስምንት | | | |

## መልመጃ 1.4

1. ከዚህ በታች በሠንጠረዥ የተሰጡትን ቁጥሮች በቁጥር ቤት ግለጽ/ጪ፡፡

| የፊደል ተራ | ቁጥር | መቶዎች | አስሮች | አንዶች |
|---|---|---|---|---|
| ሀ | 279 | | | |
| ለ | 371 | | | |
| ሐ | 807 | | | |
| መ | 923 | | | |
| ሠ | 752 | | | |
| ረ | 694 | | | |
| ሰ | 470 | | | |

2. 100 100 100 100 100 10 10 10 1 1

ሀ. ስንት መቶዎች አሉ?

ለ. ስንት አስሮች አሉ ?

ሐ. ስንት አንዶች አሉ?

መ. አንድ ላይ በአኃዝ ጻፍ/ፊ፡፡

3. ከዚህ በታች በፊደል የተሰጡትን ቁጥሮች በአኃዝ ጻፍ/ፊ፡፡

ሀ. 2 መቶዎች ፣5 አስሮች እና 4 አንዶች = ________________

ለ. 7መቶዎች፣ 2 አስሮች እና 6 አንዶች = ________________

ሐ. 4 መቶዎች ፣7 አስሮች እና 9 አንዶች = ________________

# ለ. የቁጥር ቤትን ከአባከስ እና በኩብ ማንበብና ማስቀመጥ

## ምሳሌ 10

ከዚህ በታች የተሰጠው አባከስ በቁጥር ቤት ላይ በመመስረት የተዘጋጀ ነው፡፡ በአንድ ቤት ውስጥ 4 ጨሌዎች፣ በአስር ቤት ውስጥ 2 ጨሌዎች እና በመቶ ቤት ውስጥ 3 ጨሌዎች ተቀምጠዋል፡፡




ስለዚህ 324 = 300 + 20 + 4 ይሆናል፡፡

## ምሳሌ 11

ከዚህ በታች በተሰጠው ምስል ውስጥ ስንት አስሮች እና አንዶች አሉ?



### መፍትሔ

ከላይ በተሰጠው ምስል ላይ በመመስረት 4 አስሮች እና 7 አንዶች አሉ፡፡

## ምሳሌ 12

ከዚህ በታች በተሰጠው ምስል ውስጥ ስንት አስሮች እና አንዶች አሉ?



## መፍትሔ

ከላይ በተሰጠው ምስል ላይ በመመስረት 4 አስሮች እና 9 አንዶች አሉ፡፡

## ምሳሌ 13

የካሬ ምስል በመጠቀም 247 ውስጥ ያሉ ዲጂቶችን የቁጥር ቤታቸውን ግለጽ/ጪ፡፡



| 2 መቶዎች | 4 አስሮች | 7 አንዶች |
|---|---|---|
| 200 + 40 + 7 = 247 ይሆናል፡፡ | | |

## መልመጃ 1.5

1. ከዚህ በታች ለተሰጡት ቁጥሮች አባካስ በመጠቀም ላማሳየት ለእያንዳንዱ ዲጂት በቁጥር ቤቱ ስንት ጨሌዎች እንደሚያስፈልጉ ጻፍ/ፊ፡፡

   ሀ. 518 ለ. 846

2. ሠንጠረዥ በመጠቀም ከዚህ በታች የተሰጡት ቁጥሮች ውስጥ የሚገኙ ዲጂቶችን የቁጥር ቤታቸውን ጻፍ/ፊ፡፡

   ሀ. 328 ለ. 654 ሐ. 764

**3.** ከዚህ በታች በተሰጠው ምስል ውስጥ ያሉትን የአስሮች እና የአንዶች ብዛት ጻፍ/ፊ፡፡



## 1.4 እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ እና ማነጻጸር

### ትግበራ 1.4

ከዚህ በታች የተሰጡትን ቁጥሮች “<”፣ “>” ወይም “=” ምልክቶችን በመጠቀም በመካከላቸው የሚገኙትን ዝምድና ግለጽ/ጪ፡፡

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ. 200 | | 207 | ለ. 300 | | 321 | ሐ. 630 | | 630 |

### ምሳሌ 14

ከዚህ በታች ለተሰጡት ጥንድ ጥንድ ቁጥሮች “<”፣ “>” እና “=” ምልክቶችን በመጠቀም አመዛዝን/ኚ፡፡

ሀ. 18 እና 21 ለ. 45 እና 38 ሐ. 72 እና 72 መ. 84 እና 81

### መልስ

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሀ. 18 | < | 21 | ለ. 45 | > | 38 |
| ሐ. 72 | = | 72 | መ. 84 | > | 81 |

## ምሳሌ 15

ከዚህ በታች የተሰጡትን ቁጥሮች “< ”፣ “ > ” ወይም “ = ” ምልክቶችን በመጠቀም በመካከላቸው የሚገኙትን ዝምድና ግለጽ/ጪ::

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ. 15 | 18 | ለ.105 | 98 | ሐ. 112 | 109 | መ. 688 | 714 |

### መልስ

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ. 15 | < | 18 | ለ.105 | > | 98 | ሐ.112 | > | 109 | መ.688 | < | 714 |

## አስተውል/ዪ




ሀ. በዚህ የቁጥር መስመር ላይ 212 > 211 ይሆናል:: ምክንያቱም በቁጥር መስመር ላይ በቀኝ በኩል የሚገኝ ቁጥር በስተግራው ከሚገኝ ቁጥር ይበልጣል::

ለ. በዚህ የቁጥር መስመር ላይ 214 < 216 ይሆናል:: ምክንያቱም በቁጥር መስመር ላይ በግራ በኩል የሚገኝ ቁጥር በስተቀኝ ከሚገኝ ቁጥር ሁልጊዜ ያንሳል::

## ምሳሌ 16

ከዚህ በታች ካርድ ላይ ተጽፈው የተሰጡት ቁጥሮችን ከትንሽ ወደትልቅ በቅደም ተከተል አስቀምጥ/ጪ::

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ. | 20 | 3 | 18 | 16 | 8 | 12 | 19 |
| ለ. | 25 | 38 | 19 | 53 | 44 | 61 | |

### መልስ

ሀ. 3 < 8 < 12 < 16 < 18 < 19 < 20

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ለ. | 19 | < | 25 | < | 38 | < | 44 | < | 53 | < | 61 |

## ምሳሌ 17

ከዚህ በታች ከተሰጠው ሠንጠረዥ ላይ የተሰጡትን ቁጥሮች ቅደም ተከተል በመከተል ባዶ ቦታዎቹን ሙላ/ዪ::

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2 | | | 5 | | | | 9 | | | |
| | | 15 | | | | 19 | | | | | 24 |
| 25 | | | 28 | | | | 32 | | | 35 | |
| | 38 | | | 41 | | | | 45 | | | |
| 49 | | 51 | | | 54 | | | | 58 | | 60 |

## መልስ

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 |
| 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 | 23 | 24 |
| 25 | 26 | 27 | 28 | 29 | 30 | 31 | 32 | 33 | 34 | 35 | 36 |
| 37 | 38 | 39 | 40 | 41 | 42 | 43 | 44 | 45 | 46 | 47 | 48 |
| 49 | 50 | 51 | 52 | 53 | 54 | 55 | 56 | 57 | 58 | 59 | 60 |

## መልመጃ 1.6

1. የቁጥር ጨረሮችን በመጠቀም "<" ፣ ">" ወይም "=" ምልክቶችን በባዶ ቦታው ላይ በመሙላት ሁለቱን ቁጥሮች አመዛዝን/ኚ፡፡

   ሀ. 140____142 ለ. 215____180 ሐ. 589____589

   መ. 800____900 ሠ. 301____405 ረ. 673____650

2. ከዚህ በታች የተሰጡትን በቁጥሮች ካርድ ላይ በመጻፍ በቀደም ተከተል አሳይ/ዪ::

   ሀ. 55፣ 44፣ 22፣ 33፣ 11፣ 77፣ 66፣ 99፣ 88

   ለ. 52፣ 41፣ 37፣ 24፣ 69፣ 78፣ 14፣ 82፣ 96

3. ከዚህ በታች ከተሰጠው ሠንጠረዥ ላይ የተሰጡትን ቁጥሮች ቅደም ተከተል በመጠበቅ በባዶዉ ቦታ ላይ ሙላ/ይ::

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | 72 | | | 75 | |
| 77 | | | 80 | | |
| | | 85 | | | 88 |
| | 90 | | | 93 | |
| 95 | | | 98 | | |

## ምሳሌ 18

ከዚህ በታች ለተሰጡት ቁጥሮች ቀጣያቸውን ፈልግ/ጊ::

ሀ. 9 ለ. 62 ሐ. 209 መ. 417

### መፍትሔ

| | |
|---|---|
| ሀ. 10 የ9 ቀጣይ ነው። | ለ. 63 የ62 ቀጣይ ነው። |
| ሐ. 210 የ209 ቀጣይ ነው። | መ. 418 የ417 ቀጣይ ነው። |

## ምሳሌ 19

ከዚህ በታች ለተሰጡት ቁጥሮች ቀዳሚያቸውን ፈልግ/ጊ።

ሀ. 58 ለ. 321 ሐ. 419 መ. 893

### መፍትሔ

ሀ. 57 የ58 ቀዳሚ ነው:: ለ. 320 የ321ቀዳሚ ነው::

ሐ. 418 የ419 ቀዳሚ ነው:: መ. 892 የ893 ቀዳሚ ነው::

## ምሳሌ 20

ከዚህ በታች በተሰጡት ሙሉ ቁጥሮች መካከል ያሉትን ሙሉ ቁጥሮችን ዘርዝር/ሪ።

ሀ. 109 እና 112 ለ. 54 እና 63 ሐ. 18 እና 27 መ. 69 እና 75

## መፍትሔ

ሀ. 109 እና 112

በ109 እና 112 መካከል ያሉ ሙሉ ቁጥሮች 110 እና 111 ናቸው::

ለ. 54 እና 63

በ54 እና 63 መካከል ያሉ ሙሉ ቁጥሮች 55፣ 56፣57፣ 58፣ 59፣ 60፣ 61 እና 62 ናቸው::

ሐ. 18 እና 27

በ18 እና 27 መካከል ያሉ ሙሉ ቁጥሮች 19፣ 20፣ 21፣ 22፣ 23፣ 24፣ 25 እና 26 ናቸው::

መ. 69 እና 75

በ 69 እና 75 መካከል ያሉ ሙሉ ቁጥሮች 70፣ 71፣ 72፣ 73 እና 74 ናቸው::

## መልመጃ 1.7

1. ከዚህ በታች ለተሰጡት ሙሉ ቁጥሮች ተከታያቸውን ፈልግ/ጊ::

ሀ.14 ለ.180 ሐ. 58 መ. 800 ሠ. 674 ረ. 989

2. ከዚህ በታች ለተሰጡት ሙሉ ቁጥሮች ቀዳሚያቸውን ፈልግ/ጊ::

ሀ. 58 ለ. 321 ሐ. 419 መ. 893 ሠ. 600 ረ. 901

3. ከዚህ በታች በተሰጡት ሙሉ ቁጥሮች መካከል ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ዘርዝር/ሪ::

ሀ.16 እና 21 ለ.183 እና 198 ሐ.403 እና 420

መ. 817 እና 825 ሠ.675 እና 688 ረ. 712 እና 721

| ምዕራፍ | 608 + 369 = _____ |
| --- | --- |
| 2 | 753 - 436 = _____ |

# ባለ ሶስት ዲጂት ቁጥሮችን መደመር እና መቀነስ

## 2.1 እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር

### ሀ. ያለ አለኝታ መደመር

**ትግበራ 2.1**

1. ከዚህ በታች የተሰጡትን ደምር/ሪ፡፡

ሀ. 70 + 20 = _______ ለ. 100 + 300 = _______

2. አንድ ትምህርት ቤት ከፍተኛ ነጥብ ላስመዘገቡ 200 ሴት ተማሪዎች እና 100 ወንድ ተማሪዎች ልዩ ሽልማት ሸለመ፡፡ ትምህርት ቤቱ ስንት ተማሪዎችን ሸለመ?

**ምሳሌ 1**

ሀ. 400 + 200 = _____ ለ. 800 + 100 = ______

**መልስ**

ሀ. 400 + 200 = 4 መቶዎች + 2 መቶዎች
= 6 መቶዎች
= 600 ይሆናል፡፡

ለ. 800 + 100 = 8 መቶዎች + 1 መቶ
= 9 መቶዎች
= 900 ይሆናል ፡፡

## መልመጃ 2.1

**1. ከዚህ በታች የተሰጡትን ደምር/ሪ፡፡**

ሀ. 400 + 500 = _____ ለ. 200 + 600 = _____ ሐ. 300 + 400 = ____

መ. 300 + 300 = _____ ሠ. 100 + 700 = _____ ረ. 700 + 200 = ____

2. ሞኔት የባህል ልብስ ለመግዛት በእጇዋ ካላት አምስት መቶ ብር በተጨማሪ ሶስት መቶ ብር ከባንክ ማውጣት አስፈለጋት:: ሞኔት የባህል ልብሱን በስንት ብር ገዛች?

3. ጫላ በሰኔ ወር 300 ችግኞች እና በሐምሌ ወር ደግሞ 200 ችግኞችን ተከለ፡፡ በዚህ ሁለት ወራት ውስጥ ስንት ችግኞችን ተከለ?

## ሞዴልን በመጠቀም መደመር

**ምሳሌ 2፡** 343 + 112 =_______




ስለዚህ 343 + 112 = 455 ይሆናል፡፡

## መልመጃ 2.2

የሞዴሉን ምስል በመጠቀም ደምር/ሪ፡፡

ሀ. 

ለ. 


ሐ. 


## የቁጥር ቤት ሰንጠረዥን በመጠቀም መደመር

### ምሳሌ 3

**ከዚህ በታች የተሰጡትን ድምራቸውን ፈልግ/ጊ።**

ሀ. 126 + 243 = ________ ለ. 315 + 264 =______

**መፍትሔ**

**የቁጥር ቤትን በመጠቀም መደመር**

ሀ. 126 + 243 = ________

| መቶዎች | አስሮች | አንዶች |
|---|---|---|
| 1 | 2 | 6 |
| 2 | 4 | 3 |
| | | |

| መቶዎች | አስሮች | አንዶች |
|---|---|---|
| 1 | 2 | 6 |
| 2 | 4 | 3 |
| | | 9 |

| መቶዎች | አስሮች | አንዶች |
|---|---|---|
| 1 | 2 | 6 |
| 2 | 4 | 3 |
| | 6 | 9 |

| መቶዎች | አስሮች | አንዶች |
|---|---|---|
| 1 | 2 | 6 |
| 2 | 4 | 3 |
| 3 | 6 | 9 |

ስለዚህ 126 + 243 = 369 ይሆናል፡፡

ለ. 315 + 263 =______

| መቶዎች | አስሮች | አንዶች |
|---|---|---|
| 3 | 1 | 5 |
| 2 | 6 | 3 |
| | | |

| መቶዎች | አስሮች | አንዶች |
|---|---|---|
| 3 | 1 | 5 |
| 2 | 6 | 3 |
| | | 8 |

| መቶዎች | አስሮች | አንዶች |
|---|---|---|
| 3 | 1 | 5 |
| 2 | 6 | 3 |
| | 7 | 8 |

| መቶዎች | አስሮች | አንዶች |
|---|---|---|
| 3 | 1 | 5 |
| 2 | 6 | 3 |
| 5 | 7 | 8 |

ስለዚህ 315 + 263 = 578

## መልመጃ 2.3

ከዚህ በታች ያሉትን የቁጥር ቤት ዘዴን በመጠቀም ደምር/ሪ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. 214 + 324 | ለ. 427 + 351 | ሐ. 247 + 432 | መ. 625 + 302 |
| ሠ. 833 + 142 | ረ. 712 + 84 | ሰ. 112 + 146 | ሸ. 264 + 13 |

## በቁጥር ቤት ዋጋ በመተንተን መደመር

### ትግበራ 2.2

ከዚህ በታች የተሰጡትን በቁጥር ቤት ዋጋ በመተንተን ደምር/ሪ፡፡

ሀ. 121 + 514 ለ. 491 + 108 ሐ. 762 + 35

### ምሳሌ 4

ሀ. 315 + 264=_____ ለ. 116 + 382 = _____

## መፍትሔ

ሀ. 315 + 264= _____

በመጀመሪያ የተሰጡትን ቁጥሮች በቁጥር ቤታቸው እንተነትናለን፡፡

315 = 300 + 10 + 5 እና 264 = 200 + 60 + 4

በመቀጠል ተደማሪዎችን በቁጥር ቤታቸው ዋጋ እንደምራቸዋለን፡፡

315 + 264 = 300 + 200 + 10 + 60 + 5 + 4

= 500 + 70 + 9

= 579

ለ. 116 + 382 = _____

በመጀመሪያ የተሰጡትን ቁጥሮች በቁጥር ቤታቸው እንተነትናለን፡፡

116 = 100 + 10 + 6 እና 382 = 300 + 80 + 2

በመቀጠል ተደማሪዎችን በቁጥር ቤታቸው እንደምራቸዋለን፡፡

116 + 382 = 100 + 300 + 10 + 80 + 6 + 2

= 400 + 90 + 8

=400 + 98

= 498

## መልመጃ 2.4

ከዚህ በታች የተሰጡትን በቁጥር ቤታቸው በመተንተን ደምር/ሪ ::

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. 814 + 151 | ለ. 210 + 438 | ሐ. 655 + 341 | መ. 225 + 173 |
| ሠ. 324 + 460 | ረ. 721 +146 | ሰ. 217+121 | ሸ. 453 + 146 |

## ለ. በአለኝታ መደመር

### ሞዴልን እና የቁጥር ቤትን በመጠቀም መደመር

### ትግበራ 2.3

452 ሴቶች እና 273 ወንዶች በማህበር አብረው ለመስራት ተደራጁ:: በማህበር የተደራጁት ሰዎች ብዛት ስንት ነው?

## ምሳሌ 5

194 + 451=_______







**ስለዚህ** 194 + 451 = 645 **ይሆናል ።**

**በአስር ቤት ድምር ውስጥ** 14 **አስሮችን እናገኛለን**:: 14 **አስሮች አንድ መቶ እና** 4 **አስሮች ይሆናል**:: 1 "**አንድ የመቶ** " **ቤትን ሰለሚያሳይ ወደ መቶ ቤት በመውሰድ በመቶ ቤት ላይ እንደምራለን**::

| | መቶዎች | አስሮች | አንዶች |
|---|---|---|---|
| | 1 | 9 | 4 |
| + | 4 | 5 | 1 |
| | 6 | 4 | 5 |

| መቶዎች | አስሮች | አንዶች |
|---|---|---|



## መልመጃ 2.5

ከዚህ በታች የተሰጡትን በአለኝታ ደምር/ሪ ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. 116 <br> + 342 | ለ. 290 <br> + 438 | ሐ. 653 <br> + 94 | መ. 281 <br> + 173 |
| ሠ. 526 <br> + 267 | ረ. 372 <br> + 168 | ሰ. 495 <br> + 148 | ሽ. 705 <br> + 199 |

## መሰረታዊ አልጎሪዝምን በመጠቀም መደመር

### ትግበራ 2.4

1. ከዚህ በታች የተሰጡትን ደምር/ሪ::

   ሀ. 254 + 125=_______        ለ. 619 + 326 =_______

2. ከጂማ 512 ኩንታል ቡና እና ከባሌ 460 ኩንታል ቡና ወደ ፊንፊኔ ተላከ ። በአጠቃላይ ስንት ኩንታል ቡና ወደ ፊንፊኔ ተላከ?

**ምሳሌ 6**

ከዚህ በታች የተሰጡትን ተደማሪዎች መሰረታዊ አልጎሪዝምን በመጠቀም ደምር/ሪ ።

ሀ. 263 + 512        ለ. 684 + 271

## መፍትሔ

| | |
|---|---|
| ሀ. 263<br>− 512<br>775 | በመጀመሪያ አንዶችን ደምር/ሪ 3+ 2 = 5<br>በመቀጠል አስሮችን ደምር/ሪ 6 + 1 = 7<br>በመጨረሻ መቶዎችን ደምር/ሪ 2 + 5 = 7<br>ስለዚህ775 ይሆናል። |

| | |
|---|---|
| ለ. 684<br>+ 271<br>955 | በመጀመሪያ አንዶችን ደምር/ሪ 4+1 = 5<br>በመቀጠል አስሮችን ደምር/ሪ 8+7 =15<br>በመጨረሻ መቶዎችን ደምር/ሪ 6+2 = 8<br>ስለዚህ 955 ይሆናል። |

## መልመጃ 2.6

1. ከዚህ በታች የተሰጡትን መሰረታዊ አልጎሪዝም በመጠቀም ደምር/ሪ፡፡

ሀ. 265 + 132 = _____ ለ. 391 + 455 = _____ ሐ. 619 + 162 = ____

መ. 803 + 78 = _____ ሠ. 296 + 183 = _____ ረ. 750 + 216 = ____

2. ከዚህ በታች የተሰጡትን ቁልቁል የመደመር ዘዴ በመጠቀም ደምር/ሪ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. 542<br>+ 153 | ለ. 811<br>+ 169 | ሐ. 163<br>+ 794 | መ. 173<br>+ 24 |
| ሠ. 418<br>+ 335 | ረ. 322<br>+ 161 | ሰ. 468<br>+ 174 | ሸ. 817<br>+ 99 |

# 2.2 እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ

## ሀ.ያለ ብድር መቀነስ

### ትግበራ 2.5

1.ከዚህ በታች የተሰጡትን ቀንስ/ሺ።

ሀ. 500 - 200 =_____ ለ. 700 - 300 =_____

2. በአንድ ዞን ውስጥ ተመዝግቦ የነበረው የተሽከርካሪ አደጋ 300 ነበረ። ለማህበረሰቡ ግንዛቤ ከተሰጠ በኋላ ወደ 100 ዝቅ አለ። የተሽከርካሪ አደጋ በስንት ቀነሰ?

### ምሳሌ 7

ከዚህ በታች የተሰጡትን በቁጥር ቤት በመተንተን ቀንስ/ሺ።

ሀ. 500 - 300 =_________ ለ. 900 - 400 = _________

### መልስ

ሀ. 500 - 300 = 5 መቶዎች - 3 መቶዎች

= 2 መቶዎች

= 200

ለ. 900 - 400 = 9 መቶዎች - 4 መቶዎች

= 5 መቶዎች

= 500

### መልመጃ 2.7

በቁጥር ቤት በመተንተን ቀንስ/ሺ።

ሀ. 300 - 200 = ______ ለ. 800 - 600 = ______ ሐ. 600 - 300 = ______

መ. 700 - 200 = ______ ሠ. 900 - 300 = ______ ረ. 400 - 200 = ______

## ሞዴልን በመጠቀም መቀነስ

### ምሳሌ 8

**በሞዴሎች በመጠቀም ቀነስ/ሺ፡፡**

ሀ. 435 - 10 = _____ ለ. 435 - 200 = _____

**መፍትሔ**

ሀ.







### መልመጃ 2.8

ከዚህ በታች የተሰጠውን ሞዴል በመጠቀም ቀንስ/ሺ፡፡







ሀ. ________ - ________ = ________   ለ. _____ - ______ = _________







ሐ. ________ - ________ = ________   መ. _____ - ______ = _________

## በቁጥር ቤት ዋጋ ሰንጠረዥ እና ሞዴልን በመጠቀም መቀነስ

**ምሳሌ 9**

**በቁጥር ቤት ዋጋ ሰንጠረዥ እና ሞዴልን በመጠቀም ቀንስ/ሺ፡፡**

ሀ. 573 - 422 = _______   ለ. 386 - 153 = ______

## መፍትሔ




| | መቶዎች | አስሮች | አንዶች |
|---|---|---|---|
| | 5 | 7 | 3 |
| - | 4 | 2 | 2 |
| | | | |




| | መቶዎች | አስሮች | አንዶች |
|---|---|---|---|
| | 5 | 7 | 3 |
| - | 4 | 2 | 2 |
| | | | 1 |




| | መቶዎች | አስሮች | አንዶች |
|---|---|---|---|
| | 5 | 7 | 3 |
| - | 4 | 2 | 2 |




| | መቶዎች | አስሮች | አንዶች |
|---|---|---|---|
| | 5 | 7 | 3 |
| - | 4 | 2 | 2 |
| | 1 | 5 | 1 |

## መልመጃ 2.9

**ከዚህ በታች የተሰጡትን በቁጥር ቤት ዋጋ ሰንጠረዥ እና ሞዴልን በመጠቀም ቀንስ/ሺ፡፡**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. 662 − 232 | ለ. 374 − 143 | ሐ. 965 − 754 | መ. 568 − 43 |
| ሠ. 587 − 335 | ረ. 322 − 101 | ሰ. 179 − 45 | ሸ. 583 − 479 |

# ለ. በመበደር መቀነስ

## ሞዴልን በመጠቀም መቀነስ

**ትግበራ 2.6**

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. 72 – 55 | ለ. 739 – 485 | ሐ. 506 – 354 |

**ምሳሌ 10**

438 – 276 = ______

**መፍትሔ**









ስለዚህ $438 - 276 = 162$

## መልመጃ 2.10

በመበደር ቀንስ/ሺ፡፡

ሀ. 375
− 246
______

ለ. 995
− 518
______

ሐ. 713
− 362
______

መ. 617
− 251
______

ሠ. 142
− 129
______

ረ. 727
− 518
______

ሰ. 926
− 628
______

ሸ. 201
− 154
______

## መሰረታዊ አልጎሪዝምን በመጠቀም መቀነስ

### ትግበራ 2.7

ቀንስ/ሺ ::

ሀ. $98 - 45 =$ ______ ለ. $73 - 48 =$ ______

### ምሳሌ 11

ቀንስ/ሺ::

ሀ. 249
− 114
______

ለ. 952
− 413
______

**መፍትሔ**

| | |
|---|---|
| ሀ. 249<br>- 144<br>105 | መጀመሪያ አንዶችን መቀነስ 9 – 4 = 5<br>በመቀጠል አስሮችን መቀነስ 4 – 4 = 0<br>መጨረሻም መቶዎችን መቀነስ 2 – 1 = 1<br>ስለዚህ 249 - 144 = 105 ይሆናል። |
| ለ. 954<br>- 316<br>638 | በመጀመሪያ አንዶችን እንቀንሳለን 4 - 6<br>ነገር ግን ከ4 ላየ 6ን መቀንስ ስለማይቻል ከ5 አስሮች 1 አስር ተበድረን 4 አንዶች ላይ በመደመር 14 እናገኛለን።<br>ቀጥሎ አስሮችን መቀንስ 4 - 3= 1<br>በመጨረሻም መቶዎችን መቀንስ 9- 3 =6<br>ስለዚህ 954 - 316 = 638 |

## መልመጃ 2.11

መሰረታዊ አልጎሪዝምን በመጠቀም ቀንስ/ሺ፡፡

ሀ. 714 − 102

ለ. 933 − 921

ሐ. 347 − 26

መ. 893 − 684

ሠ. 742 − 235

ረ. 326 − 168

ሰ. 460 − 54

ሸ. 801 − 429

# 2.3 መደመር እና መቀነስን የያዙ የቃላት ፕሮብሌሞች

### ትግበራ 2.8

1. በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ 635 ተማሪዎች ይማራሉ፡፡ከነዚህ ውስጥ 547 ተማሪዎች የትራፊክ ህግን ያከብራሉ፡፡ የተቀሩት በተሽከርካሪ መንገድ ላይ ቀኛቸውን ይዘው በመሄድ የትራፊክ ህግን ይጥሳሉ፡፡የትራፊክ ህግን የጣሱ ተማሪዎች ብዛት ስንት ናቸው?

2. በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ 321 ሴት ተማሪዎች እና 239 ወንድ ተማሪዎች ይማራሉ፡፡ ሁሉም ተማሪዎች ንጽህናቸውን ይጠብቃሉ፡፡ንጽህናቸውን የሚጠብቁ ተማሪዎች ብዛት ስንት ነው?

## ምሳሌ 12

1. አቶ ቶላ ሀሙስ እለት 382 እንቁላል ሸጡ፡፡ አርብ እለት ደግሞ 415 እንቁላል ሸጡ፡፡በሁለቱ ቀኖች ውስጥ ስንት እንቁላል ሸጡ?
2. በአንድ መደብር ውስጥ 947 ኩንታል ማዳበሪያ አለ፡፡784 ኩንታል ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ ከተከፋፈለ ስንት ኩንታል ማዳበሪያ ይቀራል?

## መፍትሔ

1. ሀሙስ 382 እንቁላል ሸጠ።

አርብ 415 እንቁላል ሸጠ።

በአጠቃላይ በሁለቱ ቀን የተሸጠው የእንቁላል ብዛት የሁለቱ ቀን ድምር ይሆናል፡፡ስለዚህ ከመደመር ዘዴዎች አንዱን እንጠቀማለን፡፡

| | |
|---|---|
| 382 | አንዶችን መደመር 2+5=7 |
| + 415 | አስሮችን መደመር 8+1= 9 |
| 797 | መቶዎችን መደመር 3+4=7 |
| | በሁለቱ ቀኖች 797 እንቁላሎች ተሸጡ፡፡ |

2. በመደብር ውስጥ ያለ የማዳበሪያ ብዛት በኩንታል = 947

ከመደብር ውስጥ የተከፋፈለ የማዳበሪያ ብዛት = 784

ከመደብር ውስጥ የተከፋፈለውን የማዳበሪያ ብዛት በመቀነስ ይገኛል፡፡

ስለዚህ ከመደመር ዘዴዎች አንዱን እንጠቀማለን፡፡

| | |
|---|---|
| 947<br>- 784<br>163 | አንዶችን መቀነስ 7 - 4 = 3<br>አስሮችን መቀነስ 4 - 8 ስለማይቻል አንድ አስር<br>(1 አስር) በመበደር 14 -8 = 6<br>መቶዎችን መቀነስ 8 - 7 = 1<br>ስለዚህ በመደብር ውስጥ 163 ኩነታል ማዳበሪያ ቀረ። |

## መልመጃ 2.12

ከዚህ በታች የተሰጡትን ፕሮብሌሞች አስላ/ሊ።

1. በአንድ ሱቅ ውስጥ 114 ቀይ ቀለም እርሳሶች እና 578 ጥቁር ቀለም እርሳሶች አሉ።በአጠቃላይ ስንት እርሳሶች አሉ?
2. በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ በጠዋት ፈረቃ 432 ተማሪዎች እና በከሰአት ሺፍት ደግሞ 613 ተማሪዎች ይማራሉ።ከሰአት ፈረቃ የሚማሩት ተማሪዎች በጠዋት ሺፍት የሚማሩትን በስንት የበልጣሉ?
3. በአንድ መንደር ከሚኖሩ 849 ሰዎች ውስጥ 401 ወንዶች ናቸው ።የሴቶቹ ብዛት ስንት ነው?
4. ጂሬኛ 788 ብር ከቤት ይዞ ከወጣዉ ውስጥ በ322 ብር የቤት እቃዎችን ከገዛ ስንት ብር ይቀረዋል?
5. በአንድ አጸደ ህጻናት 792 ህጻናት ይማራሉ ከነዚህ ውስጥ 396 ዶክተር መሆን ይፈልጋሉ። የተቀሩት ሁሉም መሀንዲስ መሆን ይፈልጋሉ። መሀንዲስ መሆን የሚፈልጉ ሕጻናት ብዛት ስንት ናቸው?
6. ገመዳ አንድን እቃ በ627ብር ገዝቶ 284ብር አትርፎ ሸጠ።እቃውን በስንት ሸጠ?
7. ቦንቱ በመጀመሪያ ወር 148 ብር እና በሚቀጥለው ወር ደግሞ 324 ብር ለቁጠባ አስገባች። በዚህ ሁለት ወር ውስጥ ስንት ብር ቆጠበች?
8. የአንድ እቃ ዋጋ ከሁለት ወር በፊት 415 ነበር አሁን ደግሞ 500 ሆነ። የእቃው ዋጋ በስንት ጨመረ?

9. የኢ.ፊ. ቦሩ ትምህርት ቤት ጎበዝ ተማሪዎችን በመጀመሪያው አመት 418 እና በሁለተኛው አመት 562 ከኦሮሚያ ውስጥ መርጦ ካስተማረ በሁለት አመታት ውስጥ ስንት ተማሪዎችን ያስተምራል?

10. በአንድ ደን ውስጥ 186 አንበሶች መኖራቸውን ተመዘገበ፡፡ ከአምስት አመት በኋላ ብዛታቸው 514 ደረሰ፡፡ የአንበሶቹ ብዛት በስንት ጨመረ?

# ምዕራፍ 3




# እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት

## 3.1 እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ 2 ማባዛት

### ትግበራ 3.1



1. በሳጥኑ ውስጥ ስንት የቅርጫት ኳሶች አሉ?
2. በስድስት በስድስት በቡድን ቢቀመጡ ስንት በድን ይሆናሉ?
3. $2 \times 6 =$ ___________

### ምሳሌ 1



ሁለት የብርቱካን ምድብ አለ፡፡በአንዱ ምድብ ውስጥ 3 ብርቱካን አለ፡፡በሁለቱ ምድብ ውስጥ ስንት ብርቱካን አለ?

### መፍትሔ

ሁለት የብርቱካን ምድብ አለ፡፡
ሁለት የብርቱካን ምድብ አለ፡፡ ስለዚህ $2 \times 3$ ብርቱካኖች አሉ፡፡
ብዛታቸው ደግሞ 6 ነው፡፡
ከዚህ ላይ $3 + 3 = 6$ ስለሆነ $2 \times 3 = 3 + 3 = 6$ ይሆናል፡፡

## ምሳሌ 2



ሁለት የጥንቸል ቡድን አለ፡፡ በአንድ ቡድን ውስጥ ሁለት ጥንቸሎች አሉ፡፡ በሁለቱ ቡድን ውስጥ ያሉት የጥንቸሎች ብዛት ስንት ናቸው?

**መልስ**

ሁለት የጥንቸል ቡድን አለ፡፡

በአንድ ቡድን ውስጥ ሁለት ጥንቸሎች አሉ፡፡

ስለዚህ በሁለቱ ቡድን ውስጥ ያሉት የጥንቸሎች ብዛት $2 \times 2$ ይሆናል ማለት ነው፡፡

ብዛታቸው ደግሞ 4 ነው፡፡

ከዚህ ላይ $2 + 2 = 4$ ስለሆነ $2 \times 2 = 2 + 2 = 4$

## ምሳሌ 3

በቡድን ያሉትን ምስሎች በማባዛት ግለጽ/ጪ፡፡

ሀ. 

ለ. 

**መልስ**

ሀ.  $2 \times 3 = 6$

ለ.  $2 \times 5 = 10$

## ምሳሌ 4



ወይዘሮ ተሊሌ ሁለት የተለያዩ ቦታዎችን በማዘጋጀት ችግኝ ተከሉ ፡፡ በእያንዳንዱ ቦታ ላይ 10 ችግኝ ተከሉ፡፡የተተከሉት ችግኞች ብዛት ስንት ነው?

**መልስ**

ለችግኝ የተዘጋጀ ቦታ ብዛት 2 በአንድ ቦታ ላይ ያሉ የችግኝ ብዛት 10 ስለዚህ በሁለቱም ቦታ ያሉት የችግኝ ብዛት $10 + 10 = 20$ ስለሆነም $2 \times 10 = 10 + 10 = 20$ ይሆናል

### አስተውል/ዪ

$10 \times 2 = 20$ ውስጥ

10 እና 2 የ 20አካፋዮች ናቸው::

20 ብዜት ይባላል::

## ምሳሌ 5

በተሰጠው ባዶ ሳጥን ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ጻፍ/ፊ ፡፡

ሀ. $2 \times \square = 20$ ለ. $2 \times 6 = \square$

**መልስ**

ሀ. $2 \times \boxed{10} = 20$ ለ. $2 \times 6 = \boxed{12}$

## መልመጃ 3.1

1. ከዚህ በታች የተሰጠውን የማባዛት ሠንጠረዥ ሙላ/ዪ፡፡

| × | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | | 4 | | 8 | | | 14 | | |

2. ሁለት ተማሪዎች አራት አራት ብርቱካን ገዙ፡፡ሁለቱ ተማሪዎች በአንድ ላይ ስንት ብረቱካን ገዙ?

## 3.2 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ 2 እና በ10 ማብዛት

### ትግበራ 3.2



1. በሰጥኑ ውስጥ ስንት እርሳሶች አሉ?
2. በአስር በአስር በቡድን ቢቀመጡ ስንት ቡድን ይሆናሉ?
3. የቡድኑን ብዛት በአንድ ቡድን ውስጥ ባሉ የእርሳስ ብዛት ብታባዛ/ዢ ስንት ታገኛለህ/ሽ?

**ምሳሌ 6**

አንድ አይነት ቴሌቪዥኖች በሁለት የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ ተቀምጠዋል ። በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ 6 ቴሌቪዥን ከሆነ ያለው በ 2 ቱ ክፍል ውስጥ አንድላይ ስንት ቴለተቪዥን አለ?



**መልስ**

አንድ አይነት ቴሌቪዥን በሁለት የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ ተቀምጠዋል፡፡

በእያንዳንዱ ሁለቱም ክፍሎች ውስጥ 6 ቴሌቪዥን አለ ፡፡

ስለዚህ በሁለቱ ክፍሎች ውስጥ ያለው ቴለተቪዥን 6 +6 = 12 ይሆናል፡፡

ስለዚህ 2 × 6 = 6 + 6 = 12 ይሆናል፡፡

**ምሳሌ 7**

በማባዛት አስቀምጥ/ጪ ፡፡

ሀ. 6 + 6 = ____×____ ለ. 7 + 7 + 7 +7 + 7 + 7 + 7 + 7 +7 + 7 = __× __

**መልስ**

ሀ. 6 + 6 = 2 × 6

ለ. 7 + 7 + 7 +7 + 7 + 7 + 7 + 7 +7 + 7 = 10 × 7 = 70

**ምሳሌ 8**

በ10 አባዛ/ዢ

ሀ. 10 × 1 = ______ ለ. 10 × 2 = _________

ሐ. 10 × 3 = ______ መ. 10 × 4 = _________

**መልስ**

ሀ . 10 × 1 = 10 ለ. 10 × 2 = 20

ሐ . 10 × 3 = 30 መ. 10 × 4 = 40

## መልመጃ 3.2

1. ባዶ ቦታውን በማብዛት ሙላ/ዪ

ሀ. 2 × 8=______ ለ. 2 × 12 =_____ ሐ. 2 × 15=_____

መ. 2 × 20 =______ ሠ. 2 × 28 = ______ ረ. 2 × 40 = _____

ሰ. 2 × 45 = ______ ሸ. 2 × 50 =______

2. ባዶ ቦታውን በማብዛት ሙላ/ዪ።

ሀ. 10 × 3 = _______ ለ. 10 × 4 = _____ ሐ. 10 × 5 = _____

መ. 10 × 10 =______ ሠ. 10 × 8 =______ ረ. 10 × 6 = ____

ሰ. 10 × 7 = ______ ሸ. 10 × 9=______

3. በማባዛት አስቀምጥ/ጪ።

ሀ. 8 + 8 = ___ ×___

ለ. 5 + 5 + 5 + 5 + 5 + 5 + 5+ 5 + 5 + 5 = __ × __

## 3.3 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ 0 እና በ 1 ማባዛት

### ምሳሌ 9

ከዚህ በታች የተሰጡትን ቁጥሮች በ1 አባዛ/ዢ ፡፡



አምስት አበባዎች በአንድ ምድብ ውስጥ አሉ፡፡
ብዛታቸው ደግሞ 5 ነው ፡፡
ስለዚህ $1 \times 5 = 5$

### ምሳሌ 10

ከዚህ በታች ያሉት ንቦች አበባ ላይ ናቸው፡፡በአበባው ለይ ያሉት ንቦች ብዛት ስንት ይሆናል?



### መልስ

በአበባው ላይ ያሉት ንቦች ብዛት 1 ን 7 ጊዜ ወይም $1 \times 7 = 7$ ይሆናል፡፡

### ምሳሌ 11

ከዚህ በታች የተሰጡትን ቁጥሮች በ1 በማባዛት የተሰጠውን ባዶ ቦታ ሙላ/ዪ ፡፡

| × | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | | 2 | | | 5 | | | 8 | |

### መልስ

| × | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 |

## ምሳሌ 12

ከዚህ በታች የተሰጡትን ቁጥሮች በ 0 በማባዛት ተሰጠውን ባዶ ቦታ ሙላ/ዪ ፡፡

ሀ. $0 \times 2 =$ ______ ለ. $0 \times 24 =$ ______ ሐ. $0 \times 23 =$ ______

መ. $0 \times 1 =$ ______ ሠ. $0 \times 52 =$ ______ ረ. $0 \times 35 =$ ______

## መልስ

ሀ. $0 \times 2 = 0$ ለ. $0 \times 24 = 0$ ሐ. $0 \times 23 = 0$

መ. $0 \times 1 = 0$ ሠ. $0 \times 52 = 0$ ረ. $0 \times 35 = 0$

## አስተውል/ዪ

ማንኛውም ሙሉ ቁጥር በ 0 ሲባዛ ዜሮ ይሆናል፡፡

## ምሳሌ 13

ከዚህ በታች የተሰጡትን ቁጥሮች በ 1 በማባዛት የተሰጠውን ባዶ ቦታ ሙላ/ዪ ፡፡

ሀ. $1 \times 0 =$ ______ ለ. $1 \times 5 =$ ______ ሐ. $1 \times 12 =$ ______

## መልስ

ሀ. $1 \times 0 = 0$ ለ. $1 \times 5 = 5$ ሐ. $1 \times 12 = 12$

**አስተዉል/ዪ** ማንኛውንም ሙሉ ቁጥር በ 1ካባዛን እራሱ ቁጥሩን ይሆናል::

## መልመጃ 3.3

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች በ1 አባዛ/ገር::

ሀ. 19 ለ. 28 ሐ. 42 መ. 55 ሠ. 61 ረ. 98

2. የሚከተሉትን ቁጥሮች በ 0 አባዛ/ገር::

ሀ. 7 ለ. 8 ሐ. 9 መ. 10

# 3.4 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ 3፣ 4፣ 5፣ 6፣ 7 ፣ 8 እና በ 9 ማባዛት

## ሀ. በ 3 ማባዛት

### ትግበራ 3.3

1. በእያንዳንዱ በተሰጠው ምስል ውስጥ ቀለም የተቀቡት ካሬዎች ብዛታ ስንት ይሆናል? በአጠቃላይ የተቀቡት ስንት የሆናሉ?

ሀ.



ለ.



2.



ሀ. ስንት ቡድን ዶሮዎችአሉ?

ለ. በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ ስንት ዶሮዎች አሉ?

ሐ. የቡድኑን ብዛት እና በአንድ ቡድን ውስጥ ያሉት የዶሮዎች ብዛት አንድ ላይ ሲባዙ ስንት ይሆናል?

## ምሳሌ 14

**ሀ.** 3 × 7 ን ለማግኘት የሚከተለውን ምስል ተመልከት/ቺ ፡፡



7 + 7 + 7 = 21

ስለዚህ 3 × 7 = 7 + 7 + 7 = 21 ይሆናል፡፡.

**ለ.** አንድ ሳጥን 5 ብርቱካን ይይዛል።3 የዚህ አይነት ሳጥኖች ስንት ብርቱካኖች ይይዛል?



## መልስ

አንድ ሳጥን 5 ብርቱካን ይይዛል

3 የዚህ አይነት ሳጥኖች 3 × 5 = 5 + 5 + 5 = 15 ይሆናል፡፡

## መልመጃ 3.4

**1.** የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በተሰጠህ/ሽ ምሳሌ መሰረት ሙላ/ዪ ፡፡

**ሀ.** 3 × 6 = 6 + 6 + 6 = 18

**ለ.** 3 × 14 = ________ + ________ + ________ = ________

**ሐ.** 3 × 23 = ________ + ________ + ________ = ________

መ. 3 × 25 = ________ + _________ + ________ = ________

ሠ. 3 × 12 = ________ + _________ + ________ = ________

2. ከዚህ በታች የተሰጠውን የማባዛት ሰንጠረዥ ሙላ/ዪ ፡፡

| × | 14 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 | 23 | 24 | 25 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3 | | 48 | | | | 60 | | | 69 | | |

3. የ3 ብዜቶችን እስከ 20 ያሉትን ዘርዝር/ሪ፡፡

4. አንድ ሳጥን 21ብርቱካን ይይዛል:: 3 የዚህ አይነት ሳጥኖች ስንት ብርቱካኖች ይይዛል?

## ለ. በ 4 ማባዛት

### ትግበራ 3.4

ሶስት ሶስት ዶሮዎች በአራት ቦታ ተቀመጠዋል፡፡ባንድ ላይ ብንቆጥራቸው ስንት ይሆናሉ?



### ምሳሌ 15

1. የሚከተለውን የማባዛት ሠንጠረዥ በ 4 በማባዛት ፈልግ/ጊ፡፡

| × | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | 4 | | 12 | | | | 28 | | |

**መልስ**

| × | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | 4 | 8 | 12 | 16 | 20 | 24 | 28 | 32 | 36 |

## ምሳሌ 16



የሚከተለው ሠንጠረዥ ላይ በመመስረት አግድም እና ቁልቁል ያሉ የአበቦች ምስል ብዛት ስንት ይሆናል ? አጠቃላይ ብዛታቸው ስንት ይሆናል ?

**መልስ**

አግድም ያሉ አበቦች ምስል ብዛት 4
ቁልቁል ያሉ አበቦች ምስል ብዛት 3
አጠቃላይ የአበቦች ምስልብዛት
$4 \times 3 = 12$

## መልመጃ 3.5

1. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በተሰጠህ/ሽ ምሳሌ መሰረት ሙላ/ዪ ፡፡
   ሀ. $4 \times 9 = 9 + 9 + 9 + 9 = 36$
   ለ. $4 \times 13 =$ _____ + _____ + _____ + ______ = ______
   ሐ. $4 \times 15 =$ _____ + _____ + _____ + ______ = ______
   መ. $4 \times 22 =$ _____ + _____ + _____ + ______ = ______

2. የሚከተለውን የማባዛት ሠንጠረዥ በተሰጠህ/ሽ ምሳሌ መሰረት ሙላ/ዪ ፡፡

| × | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 | 23 | 24 | 25 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | 60 | | 68 | | 76 | | | 88 | | | 100 |

3. የ4 ን ብዜቶች እስከ 48 ያሉትን ዘርዝር/ሪ ፡፡

# ሐ. በ 5 ማባዛት

## ምሳሌ 17

ሶስት አፕሎች በሶስት ሶስት በአምስት ቦታ አሉ ባንድላይ ስንቆጥራቸው ስንት ይሆናሉ?



$5 \times 3 = 3 + 3 + 3 + 3 + 3 = 15$

## ምሳሌ 18

**የሚከተለውን የማባዛት ሠንጠረዥ ሙሉ/ዪ ፡፡**

| × | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | | | 85 | | | 100 |

## መልስ

| × | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | 75 | 80 | 85 | 90 | 95 | 100 |

## ምሳሌ 19

**የሚከተሉት ቁጥሮች በ 5 ሲባዙ ስንት የሆናሉ?**

ሀ. 6 ለ. 4 ሐ. 12 መ. 20

## መልስ

**ሀ.** $5 \times 6 =$ ________

$5 \times 6 = 6 + 6 + 6 + 6 + 6 = 30$

**ለ.** $5 \times 4 =$ ________

$5 \times 4 = 4 + 4 + 4 + 4 + 4 = 20$

**ሐ.** $5 \times 12 =$ ______

$5 \times 12 = 12 + 12 + 12 + 12 + 12 = 60$

**መ.** $5 \times 20 =$ ______

$5 \times 20 = 100$

## መልመጃ 3.6

1. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በተሰጠህ/ሽ ምሳሌ መሰረት ሙላ/ዪ ፡፡

   ሀ. $5 \times 7 = 7 + 7 + 7 + 7 + 7 = 35$

   ለ. $5 \times 8 =$ ________ + ______ +______ + ______+ ______= ________

   ሐ. $5 \times 9 =$ ________ + ______ +______ + ______+ ______= ________

   መ. $5 \times 10 =$ ________ + ______ +______ + ______+ ______= ________

   ሠ. $5 \times 11 =$ ________ + ______ +______ + ______+ ______= ________

2. የ5 ን ብዜቶች እስከ 96 ያሉትን ዘርዝር/ሪ፡፡

3. የአንድ እርሳስ ዋጋ 5 ብር ከሆነ የዚሁ አይነት አራት እርሳስ ስንት ብር ያወጣል?

# መ. በ 6 ማባዛት

## ትግበራ 3.5

$6 \times 4$ ወደ መደመር በመቀየር በቡድን ተወያይታችሁ ስሩ፡፡

### ምሳሌ 20

ሀ. $6 \times 3 =$ ____________

### መልስ

$6 \times 3$ ስንት እንደሆነ ለማግኘት ከዚህ በታች የተሰጡትን ወፎች አንድ ላይ በመደባለቅ ቁጠር/ሪ፡፡



$3 + 3 + 3 + 3 + 3 + 3 = 18$

ስለዚህ $6 \times 3 = 18$ ይሆናል፡፡

ለ. $6 \times 7 =$ ____________

## መልስ

$6 \times 7 = 7 + 7 + 7 + 7 + 7 + 7 = 42$

ስለዚህ $7 \times 6 = 42$

## መልመጃ 3.7

1. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በተሰጠህ/ሽ ምሳሌ መሰረት ሙላ/ዪ፡፡

   ሀ. $6 \times 6 = 6 + 6 + 6 + 6 + 6 + 6 = 36$

   ለ. $6 \times 8 =$ _____ + _____ + _____ + _____ + _____ + _____ = ______

   ሐ. $6 \times 10 =$ _____ + _____ + _____ + _____ + _____ + _____ = __ __

   መ. $6 \times 11 =$ _____ + _____ + _____ + _____ + _____ + _____ = ______

   ሠ. $6 \times 12 =$ _____ + _____ + _____ + _____ + _____ + _____ = ______

2. የ6 ን ብዜቶች እስከ 48 ያሉትን ዘርዝር/ሪ፡፡

3. አንድ ሳጥን 7 ብርቱካኖች መያዝ ይቻላል፡፡ የዚሁ አይነት 6 ሣጥን ስንት ብርቱካን ይይዛል?

# ሠ.በ 7 ማባዛት

## ትግበራ 3.6

ፈዬራ 7 በቡድን የሚጋልቡ ፈረሶች ተመለከተ፡፡ ሰባቱም ቡድኖች ሁለት ሁለት ፈረሶች ያላቸው ከሆነ በአጠቃላይ ፈዬራ ስንት ፈረሶች ተመለከተ?



## ምሳሌ 21

ሀ. $7 \times 4 =$ ________ ለ. $7 \times 5 =$ ________ ሐ. $7 \times 6 =$ ________

### መልስ

ሀ. $7 \times 4 =$ ________

$7 \times 4 = 4 + 4 + 4 + 4 + 4 + 4 + 4 = 28$

ስለዚህ $7 \times 4 = 28$

ለ. $7 \times 5 =$ ________

$7 \times 5 = 5 + 5 + 5 + 5 + 5 + 5 + 5 = 35$

ስለዚህ $7 \times 5 = 35$

ሐ. $7 \times 6 =$ ________

$7 \times 6 = 6 + 6 + 6 + 6 + 6 + 6 + 6 = 42$

ስለዚህ $7 \times 6 = 42$

## ምሳሌ 22

የሚከተለውን ባዶ ቦታ በትክክለኛ መልስ ሙላ/ዪ፡፡

ሀ. $7 \times$ ____ $= 35$ ለ. ____ $\times 8 = 56$ ሐ. $6 \times$ ____ $= 54$

መ. $7 \times$ ____ $= 84$ ሠ. ____ $\times 11 = 77$ ረ. $6 \times$ ____ $= 90$

### መልስ

ሀ. $7 \times 5 = 35$ ለ. $7 \times 8 = 56$ ሐ. $6 \times 9 = 54$

መ. $7 \times 12 = 84$ ሠ. $7 \times 11 = 77$ ረ. $6 \times 15 = 90$

## መልመጃ 3.8

1. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በተሰጠህ/ሽ ምሳሌ መሰረት ሙላ/ዪ፡፡

ሀ. $7 \times 6 = 6 + 6 + 6 + 6 + 6 + 6 + 6 = 42$

ለ. $7 \times 8 =$ ____ + ____ + ____ + ____ + ____ + ____ + ____ = ______

ሐ. $7 \times 9 =$ ____ + ____ + ____ + ____ + ____ + ____ + ____ = ______

መ. $7 \times 10 =$ ____ + ____ + ____ + ____ + ____ + ____ + ____ = ______

ሠ. $7 \times 11 =$ _____ + _____ + _____ + _____ + _____ + _____ + _____ = ______

ረ. $7 \times 12 =$ _____ + _____ + _____ + _____ + _____ + _____ + _____ = ______

2. የ 7 ን ብዜቶች እስከ 49 ያሉትን ዘርዝር/ሪ፡፡

3. የሚከተለውን ባዶ ቦታ በትክክለኛ መልስ ሙላ/ዪ፡፡

ሀ. $7 \times$ _____ $= 21$ ለ. _____ $\times 9 = 63$ ሐ. $7 \times$ _____ $= 14$

መ. $7 \times$ _____ $= 98$ ሠ. _____ $\times 1 = 7$ ረ. $7 \times$ _____ $= 35$

## ረ. በ 8 ማባዛት

### ትግበራ 3.7

$8 \times 4$ በመደመር አሳይ/ዪ፡፡

### ምሳሌ 23

አባዛ/ዢ

ሀ. $8 \times 3 =$ _______ ለ. $8 \times 9 =$ _______

**መልስ**

ሀ. $8 \times 3 = 3 + 3 + 3 + 3 + 3 + 3 + 3 + 3 = 24$

ስለዚህ $3 \times 8 = 24$

ለ. $8 \times 9 = 9 + 9 + 9 + 9 + 9 + 9 + 9 + 9 = 72$

ስለዚህ $8 \times 9 = 72$

### ምሳሌ 24

የሚከተለውን ባዶ ቦታ በስንት ቁጥር ብትሞላ/ዪ የተሰጠውን ብዜትታገኛለህ/ሽ?

ሀ. $8 \times$ _____ $= 24$ ለ. $8 \times$ _____ $= 72$ ሐ. $8 \times$ _____ $= 32$

**መልስ**

ሀ. $8 \times 3 = 24$ ለ. $8 \times 9 = 72$ ሐ. $8 \times 4 = 32$

### መልመጃ 3.9

1. ከዚህ በታች የተሰጠውን ባዶ ቦታ ሁለቱን ቁጥሮች በማባዛት ሙላ/ዪ፡፡

ሀ. 8 × 5 = _____ ለ. 8 × 6 = _____ ሐ. 8 × 7 = _____

መ. 8 × 11 = ____ ሠ. 8 × 12 = _____

2. በማባዛት የሚከተለውን ሠንጠረዥ ሙላ/ዪ፡፡

| × | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 8 | | | 24 | | | | | 64 | | | |

3. የ8ን ብዜቶች እስከ 64 ያሉትን ዘርዝር፡፡

4. የአንድ እንቁላል ዋጋ 8 ብር ነው፡፡ የዚህ አይነት 10 እንቁላል ስንት ብር ነው?

5. የሚከተለውን ባዶ ቦታ በትክክለኛ መልስ ሙላ/ዪ፡፡

ሀ. 8 × _____ = 64 ለ. _____ × 10 = 80 ሐ. 8 × _____ = 96

# ሰ. በ 9 ማባዛት

## ትግበራ 3.8

የሚከተለውን የማባዛት ሠንጠረዥ በተሰጠህ/ሽ ምሳሌ መሰረት ሙላ/ዪ፡፡

| × | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 9 | | 18 | | | 45 | | | | | 90 |

**ምሳሌ 25**

**አባዛ/ዢ**

ሀ. 9 × 3 = _________ ለ. 9 × 10 = _______

**መልስ**

ሀ. 9 × 3 = 3 + 3 + 3 + 3 + 3 + 3 + 3 + 3 + 3 = 27

ስለዚህ 9 × 3 = 27

ለ. 9 × 10 = _______

9 × 10 = 10 + 10 + 10 + 10 + 10 + 10 + 10 + 10 + 10 = 90

ስለዚህ 9 × 10 = 90

## መልመጃ 3.10

1. ከዚህ በታች የተሰጡትን የቁጥሮች ብዜት ባዶ ቦታው ላይ ሙላ/ዪ፡፡

ሀ. 9 × 4 = _____ ለ. 9 × 5 = _____ ሐ. 9 × 6 = _____

መ. 9 × 7 = _____ ሠ. 9 × 8 = _____ ረ. 9 × 10 = _____

2. የ9ን ብዜቶች እስከ 81 ያሉትን ዘርዝር፡፡
3. አንድ ብርቱካን በ 9ብር ተገዛ፡፡ እንደዚሁ አይነት 10 ብርቱካን በስንት ብር ይገዛል?
4. የሚከተለውን የማባዛት ሠንጠረዥ ሙላ/ዪ፡፡

| × | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | | 5 | | | | | |
| 2 | | 4 | | | | | | | | |
| 3 | | | | | | 18 | | | | |
| 4 | | | | | | | | 32 | | |
| 5 | | | | | | | | | | 50 |
| 6 | | | | | | | | | 54 | |
| 7 | | | | 28 | | | | | | |
| 8 | | | | | | | 56 | | | |
| 9 | | | 27 | | | | | | | |
| 10 | 10 | | | | | | | | | |

5. የሚከተለዉን ባዶ ሳጥን በትክክለኛ መልስ ሙላ/ዪ፡፡

ሀ. ☐ × 9 = 27 ለ. 9 × ☐ = 36 ሐ. ☐ × 10 = 90

መ. ☐ × 9 = 99 ሠ. 7 × ☐ = 63 ረ. ☐ × 8 = 72

# 3.5 የቃላት ፕሮብሌሞች

## ምሳሌ 26

1. ወይዘሮ ደራርቱ 7 ልጆች አላት፡፡ ለእያንዳንዳቸው ዘጠኝ ዘጠኝ የቡና ችግኝ እንዲተክሉ አከፋፈለች፡፡ ወይዘሮ ደራርቱ ስንት ችግኝ ለልጆቿ አከፋፈለች?

### መፍትሔ

የልጆች ብዛት 7

ወይዘሮ ደራርቱ ለእያንዳንዳቸው የከፋፈለችው የቡና ችግኝ ብዛት 9

ወይዘሮ ደራርቱ ያከፋፈሉት ችግኝ ብዛት $= 7 \times 9 = 63$ ይሆናል፡፡

2. ለሊሳ እና ወንድሞቹ 6 ናቸው፡፡ብርቱካን ሲከፋፈሉ ስምንት ስምንት ደረሳቸው፡፡ በአጠቃላይ ስንት ብርቱካን ነው የተከፋፈሉት?

### መፍትሔ

የለሊሳ ወንድሞች ብዛት 6

ለአንድ ሰው የደረሰው ብርቱካን ብዛት 8

ለሊሳ እና ወንድሞቹ የተከፋፈሉት ብዛት $7 \times 8 = 56$ ይሆናል፡፡

## መልመጃ 3.11

1. የአንደኛ ሀ ክፍል ሂሳብ መምህርት የክፍሏን ተማሪዎች እኩል 8 ቦታ ከፍላ የቡድን ስራ ሰጠቻቸው፡፡ አንዱ ቡድን ውስጥ 4 ተማሪዎች ከያዘ የ አንደኛ ሀ ክፍል ተማሪዎች ብዛት ስንት ናቸው?
2. ወይዘሮ ተሊሌ ለአምስት ልጆቿ አራት አራት ደብተር ገዛች፡፡ ወይዘሮ ተሊሌ ስንት ደብተር ገዛች?
3. ሲምቦ ፣ ዱሬቲ እና ጋዲሴ በሂሳብ ትምህርት ከፍተኛ ነጥብ አስመዘገቡ፡፡ መምህርታቸው ጫልቱ ለያነዳንዳቸው አራት አራት ደብተር ሽልማት ሰጠቻቸው፡፡ በአጠቃላይ ስንት ደብተር ተሸለሙ?

# ምዕራፍ 4




# ግማሾች እና ሩቦች

## 4.1 ግማሾች

### ሀ. አንድን ሙሉ ነገር ሁለት እኩል ቦታ በመክፈል ግማሽን ማሳየት

**ትግበራ 4.1**

1. አንድን ዳቦ ሁለት እኩል ቦታ ክፍለህ/ሽ አንዱን ብትበላ/ዪ ስንት እጅ ይቀራል?
2. አንድ የሬክታንግል ቅርፅ ያለዉ ወረቀት ሁለት እኩል ቦታ በማጠፍ በአንድ በኩል በእርሳስ ቀባ/ቢ:: ይህ የተቀባው ምን ያሳያል?

**አስተውል/ይ**

ግማሽ የሚገኘው አንድ ሙሉ ነገር ሁለት እኩል ቦታ ሲከፈል ነው::

**ምሳሌ 1**

1. አንድን ብርቱካን ሁለት እኩል ቦታ ክፍለህ/ሽ አንዱን ብትበላ/ይ ስንት እጅ ይቀራል?



## መፍትሔ

| | |
|---|---|
|  | አንድን ብርቱካን ሁለት እኩል ቦታ ከፍለህ/ሽ አንዱን ከበላህ/ሽ የሚቀረው የብርቱካኑ **ግማሽ** ይሆናል:: |

## ምሳሌ 2

አቶ ለሚ ለሁለት ልጆቹ አንድን ዳቦ ሁለት እኩል ቦታ ከፍሎ ሰጣቸው:: የእያንዳንዱ የልጆቹ ድርሻ ምን ያህል ይሆናል?

| | |
|---|---|
|  | **መልስ፤** የልጆቹ የእያንዳንዱ ድርሻ የዳቦው **ግማሽ** ይሆናል::  |

## ምሳሌ 3

ከታች በተሰጠው የክብ ምስል ላይ የተቀባው ምን ያህሉ ክፍል ነው? የተቀባውስ ምን ይባላል?



## መልስ

በክቡ ምስል ላይ የተቀባው ከሁለቱ እኩል ክፍሎች አንዱ ክፍል ብቻ ነው:: ይህ የተቀባዉ ክፍል የክቡ **ግማሽ** ይባላል::

## ምሳሌ 4

ከታች በተሰጠው የሬክታንግል ምስል ላይ የተቀባው ምን ያህሉ ክፍል ነው? የተቀባውስ ምን ይባላል?



## መልስ

በሬክታንግሉ ምስል ላይ የተቀባው ከሁለቱ እኩል ክፍሎች አንዱ ክፍል ብቻ ነው:: ይህ የተቀባዉ ክፍል የሬክታንግሉ **ግማሽ** ይባላል::

## ምሳሌ 5

ከአንድ ሎሚ የተከፈሉ ሁለት ግማሽ ሎሚዎች አንድ ላይ መልሰው ቢጋጠሙ ምን ያህል ይሆናሉ?

## መፍትሄ

ሁለት ግማሽ ሎሚዎች አንድ ላይ መልሰው ቢጋጠሙ አንድ ሙሉ ሎሚ ይሆናሉ::




## ምሳሌ 6

ከዚህ በታች በክቡ ምስል ላይ የተቀባው የክቡ **ግማሽ** ሊሆን ይችላል?



## መልስ

በክቡ ምስል ላይ የተቀባው የክቡ ግማሽ አይደለም::

## መልመጃ 4.1

1. ከታች የተሰጡትን ምስሎች ግማሾቻቸውን አጥቁር/ሪ::

ሀ.  ለ.  ሐ. 

2. ከታች የተሰጡትን ምስሎች በእርሳስ ሁለት እኩለ ቦታ በመክፈል ግማሾቻቸውን ቀባ/ቢ::

ሀ.  ለ.  ሐ.  መ. 

## ለ. ብዛቱ ሙሉ ቁጥር የሆነን ነገር ሁለት እኩል ቦታ በመክፈል ግማሽን ማሳየት

### ምሳሌ 7

ቦንቱ እና ጫላ የተሰጠውን አናናስ ተራ በተራ አንድ አንድ እየተካፈሉ ከሄዱ ስንት ስንት አናናስ ይደርሳቸዋል?



### መፍትሔ

የተሰጠው የአናናስ ብዛት 10 ነው:: ተራ በተራ አንድ አንድ ሲካፈሉ እያንዳንዳቸው አምስት አምስት አናናስ ይደርሳቸዋል::



የቦንቱ ድርሻ      የጫላ ድርሻ

ስለዚህ የአስር ግማሽ አምስት ይሆናል::

## ምሳሌ 8

ከዚህ በታች በተሰጠው የልጆች ምስል በቅደም ተከተል መጀመሪያ ሴት ቀጥሎ ወንድ በሚል ላይ በመመስረት ጥያቄዎቹን መልስ/ሺ::

ሀ. አጠቃላይ የልጆቹ ምስል ብዛት ስንት ነው?

ለ. የሴት ልጆች ምስል ብዛት ስንት ነው?

ሐ. የወንድ ልጆች ምስል ብዛት ስንት ነው?



## መልስ

ሀ. በአጠቃላይ የልጆቹ ምስል ብዛት ስምንት ነው::

| | |
|---|---|
| ለ. የሴት ልጆች ምስል ብዛት 4 ነው:: ይህም የአጠቃላይ የልጆቹ ምስል ብዛት ግማሽ ነው:: |  |
| ሐ. የወንድ ልጆች ምስል ብዛት 4 ነው:: ይህም የአጠቃላይ የልጆቹ ምስል ብዛት ግማሽ ነው:: |  |

## ምሳሌ 9

በቁጥር መስመሩ ላይ 0 እና 2 መካከል የተቀባው ምን ይባላል?



## መልስ

በ1 እና 2 መካከል ያለው ርቀት በ0 እና 2 መካከል ያለው ርቀት **ግማሽ** ነው። ያልተቀባው በ0 እና 1 መካከል ያለው ርቀት በ0 እና 2 መካከል ያለው ርቀት **ግማሽ** ነው።




## መልመጃ 4.2

1. በቁጥር መስመሩ ላይ 0 እና 4 መካከል የተቀባው ምን ይባላል?




2. በአንድ ክፍል ውስጥ ካሉት 40 ተማሪዎች ውስጥ የሴቶች ብዛት 20 ቢሆን የወንዶች ብዛት ______________የአጠቃላይ የተማሪዎቹ ብዛት ይሆናል::
3. ሜቲ እና ፍሮምሳ ከታች የተሰጠውን ብርቱካን እኩል ተከፋፈሉ።

ሀ. የሜቲ ድርሻ ምን ያህል ነው? የፍሮምሳ ድርሻስ?

ለ. የሜቲ ድርሻ ____________የአጠቃላይ የብርቱካኖቹ ብዛት ይሆናል::



# 4.2 ሩቦች

## ሀ. ሙሉ የሆነን ነገር አራት እኩል ቦታ በመክፈል ሩብን ማሳየት

### ትግበራ 4.2

አንድ ሬክታንግል ቅርጽ ያለው ምስል አራት እኩል ቦታ በመክፈል አንዱ ተቀባ:: የተቀባው የሬክታንግሉ አካል ምን ተብሎ ይጠራል?

## አስተውል/ዪ

ሩብን የምናገኘው አንድን ሙሉ ነገር **አራት** እኩል ቦታ ስንከፍል ነው::

ሲሶን የምናገኘው ደግሞ አንድን ሙሉ ነገር **ሶስት** እኩል ቦታ ስንከፍል ነው::

### ምሳሌ 10

ከዚህ በታች ያለው የክብ ምስል በምን ያህል ክፍሎች ተከፍሏል? ምን ያህሉ ክፍል ተቃባ? የተቀባው ምን ይባላል?



### መልስ

የተሰጠው የክብ ምስል አራት እኩል ቦታ ተከፍሏል:: ካሉት አራት ክፍሎች መካከል የተቀባው አንዱ ክፍል ብቻ ነው:: ይህ የተቀባው ክፍል ሩብ ይባላል::

### ምሳሌ 11

አቶ ሰኚ ለአራት ልጆቹ አንድ ብርቱካን አራት እኩል ቦታ አካፈለላቸው::

የእያንዳንዱ ልጅ ድርሻ ምን ያህል ነው?

### መፍትሔ

| | |
|---|---|
|  | አቶ ሰኚ ለአራት ልጆቹ አንድ ብርቱካን አራት እኩል ቦታ አካፈለላቸው:: |
|  | የእያንዳንዱ የአቶ ሰኚ ልጆች ድርሻ የብርቱካኑ ሩብ ይሆናል:: |

## ምሳሌ 12

ከዚህ በታች ያለው የካሬ ምስል በስንት ክፍሎች የተከፈለ ነው? ምን ያህሉ ክፍል ተቀባ? የተቀባውስ ምን ይባላል?



## መልስ

የተሰጠው የካሬ ምስል በአራት ክፍሎች ተከፍሏል:: ከአራቱ ክፍሎች ውስጥ የተቀባው አንዱ ክፍል ብቻ ነው:: ይህ የተቀባው የካሬ ክፍል ሩብ ይባላል::

## ምሳሌ 13

ከዚህ በታች ያለው የካሬ ምስል በስንት እኩል ክፍሎች የተከፈለ ነው? ምን ያህሉ ክፍል ተቀባ? የተቀባውስ ምን ይባላል?



## መልስ

የተሰጠው የካሬ ምስል በአራት እኩል ክፍሎች ተከፍሏል:: ከአራቱ ክፍሎች የተቀቡት ሁለቱ ብቻ ናቸው:: ይህ የተቀባው የካሬ ክፍል ግማሽ ይባላል::

## መልመጃ 4.3

1. ከዚህ በታች ያሉትን ምስሎች ሩባቸውን ቀባ/ቢ::

ሀ. 

ለ. 

2. ከዚህ በታች ያሉትን ምስሎች እርሳስ በመጠቀም አራት እኩል ቦታ በመክፈል አንዱን ቀባ/ቢ::

ሀ. 

ለ. 

3. ከዚህ በታች ለተሰጡት ዓረፍተነገሮች ባዶ ቦታቸውን በ‘‘<’’፣ ‘‘>’’ ወይም ‘‘ =’’ ምልክት በመሙላት አነጻጽር/ሪ::

ሀ. ግማሽ ____________ ሙሉ.

ለ. ሩብ ________ሲሶ

ሐ. ሲሶ ______________ግማሽ

መ. ሩብ ________ግማሽ

ሠ. ሙሉ ______________ሲሶ

ረ. ሩብ _________ሙሉ

## ለ. ብዛቱ ሙሉ ቁጥር የሆነን ነገር አራት እኩል ቦታ በመክፈል ሩብን ማሳየት

### ምሳሌ 14

ከዚህ በታች ባለው የቁጥር መስመር ላይ በተሰጡት ቁጥሮች መካከል የተቀባዉ ክፍል ለመስመሩ ሙሉ ርዝመት ምን ይባላል?

ሀ. 0 እና 1 ለ. 1 እና 2 ሐ. 2 እና 3 መ. 3 እና 4




### መልስ

ሀ. በ0 እና 1 መካከል የተቀባው ሩብ ወይም አንደኛ ሩብ ይባላል::

ለ. 1 እና 2 መካከል የተቀባው ሩብ ወይም ሁለተኛ ሩብ ይባላል::

ሐ. 2 እና 3 መካከል የተቀባው ሩብ ወይም ሶስተኛ ሩብ ይባላል::

መ. 3 እና 4 መካከል የተቀባው ሩብ ወይም አራተኛ ሩብ ይባላል::




| | | | |
|---|---|---|---|
| አንደኛ | ሁለተኛ | ሶስተኛ | አራተኛ |

## ምሳሌ 15

ጫልቱ ስምንት እንቁላል አላት:: ለሶስት ጓደኞቿ ሁለት ሁለት እንቁላል ከሰጠቻቸው ለእሷ ስንት እንቁላል ይቀሪላታል?



## መልስ

ለእያንዳንዳቸው ሶስት ጓደኞቿ ሩብ ይደርሳቸዋል እና ለእሷም ደግሞ ሩብ ይቀርላታል::



## ምሳሌ 16

ጫላ ዘጠኝ አፕሎች አሉት:: የዘጠኙን አፕሎች ሲሶ ለእህቱ አካፈለ:: ጫላ ስንት አፕሎችን ለእህቱ አካፈለ?



## መልስ

ሲሶ አንድ ነገርን ሶስት እኩል ቦታ በመክፈል ይገኛል:: ይህም ጫላ 9 አፕሎችን በሲሶ ሲያካፍል 3ይሆናል::

ስለዚህ የጫላ እህት 3አፕሎችን ወይም የ9አፕሎችን ሲሶ ተካፈለች::

## ምሳሌ 17

ከአራት መኪኖች መካከል አራቱ ቀይ እና ሁለቱ ደግሞ ነጭ ናቸው:: የትኛው ሙሉን ያሳያል? የትኛው የሙሉ ክፍልን ያሳያል?




## መልመጃ 4.4

1. መርጋ 20ችግኞችን ተከለ። ችግኞቹ ዋንዛ፣ ሾላ፣ ባህርዛፍ እና ዝግባ ናቸው። ከተተከሉ ችግኞች ውስጥ 5ቱ ሾላ፣ 5ቱ ባህርዛፍ እና 5ቱ ዝግባ ናቸው። ከዚህ በታች የተሰጡትን ጥያቄዎች መልስ/ሺ።

   ሀ. የዋንዛ ብዛት የ20_________ነው።

   ለ. የሾላ ብዛት የ20_________ነው።

   ሐ. የሾላ ብዛት እና የዝግባ ብዛት የ20 _________ነው።

   መ. የባህርዛፍ ብዛት እና የዋንዛ የ20_________ነው።

2. ከዚህ በታች የተሰጡትን አስላ/ዪ።

   ሀ. ሩብ + ሩብ = _____________     ለ. ሩብ + ሩብ + ሩብ + ሩብ =__________

3. ጫልቱ እና መገርቱ እኩል የሆኑ የተለያዩ ወረቀት ለየብቻ አላቸው። ጫልቱ ወረቀቷን እኩል አራት ቦታ ቆረጠችው። መገርቱ ደግሞ ወረቀቷን እኩል ሁለት ቦታ ቆረጠችው። ብዙ የወረቀት ቁራጭ ያለው ማን ነው? ትልልቅ የወረቀት ቁራጭ ያለውስ ማን ነው?

4. ሶሬቲ አንድን የክብ ግማሽ አረንጓዴ ቀለም ሁለቱን ሩቦች ጥቁር እና ነጭ ቀባች። ሶሬቲ የምትፈልገው ክብ ከዚህ በታች ካሉት ውስጥ የትኛው ነው?

ሀ. 

ለ. 

ሐ. 

መ. 

5. ከዚህ በታች የተሰጠው ምስል ስንት ቦታ ተከፋፍሏል? ምን ያህሉ ክፍል የተቀባ ነው? የተቀባው ምን ይባላል?

ሀ. 

ለ. 

መ. 

ሠ. 

ረ. 

# ምዕራፍ 5



# ፓተርኖች

## 5.1 የድግግሞሽ ዩኒት

### ትግበራ 5.1

ከዚህ በታች የተሰጠው ምስል ተማሪዎች የተለያዩ ቀለም ያላቸውን ካርዶች እንዴት በቅደም ተከተል እንደሚያስቀምጡ ያሳያል:: ተማሪዎች እናንተም የተለያዩ ቀለም ያላቸውን ካርዶች በመደጋገም በቅደም ተከተል አስቀምጡ።



**አስተውል/ይ**

የነገሮች አቀማመጥ የተቀናጀ ድግግሞሽ መልክ ያለው ከሆነ ፓተርን ይባላል። በዚህ የነገሮች አቀማመጥ ውስጥ ያለቸው የድግግሞሽ የተራ መጠን የድግግሞሽ ዩኒት ይባላል::

## ምሳሌ 1

የተደጋገመ ፓተርን የሆነው የቱ ነው?




## መልስ

1. አንድ አይነት የጎነ-ሶስቶች ድግግሞሽ አለ:: ስለዚህ ፓተርን ነው::
2. ጎነ-አራት እና ሞላላ ቋሚ ድግግሞሽ አላቸው:: ስለዚህ ፓተርን ነው::
3. አንድ ጎነ-ሶስት እና አንድ ዲያመንድ ቋሚ ድግግሞሽ አላቸው:: ስለዚህ ፓተርን ነው::
4. ሶስት ምስሎች ተራ በተራ ተደጋግመዋል:: ስለዚህ ፓተርን ነው::

## ምሳሌ 2

ከዚህ በታች ያሉት ፓተርኖች ከስንት ዩኒት እንደ ተሰሩ ግለጽ/ጪ::




## መልስ

1. አረንጓዴ እና ቢጫ ቀለሞች በተከታታይ ተራ በተራ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ተቀብተዋል። ስለዚህ ባለ2 ዩኒት ፓተርን ነው።

2. ባለቀይ መስመር ጎነ-አራት እና ተከታታይ ነጥቦች ተራ በተራ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ተቀምጠዋል፡፡ ስለዚህ ባለ2 ዩኒት ፓተርን ነው፡፡

3. ከክብ እና ከካሬ የተሰራ ፓተርን ነው፡፡ስለዚህ ባለ2 ዩኒት ፓተርን ነው፡፡

## መልመጃ 5.1

1. ከዚህ በታች ከተሰጡት ውስጥ ፓተርን ያልሆነውን ለይ/ዩ::

ሀ. 

ለ. 

ሐ. 

መ. 

ሠ. 

ረ. 

2. ከዚህ በታች የተሰጡት ፓተርኖች ከስንት አነስተኛ ዩኒቶች እንደተሰሩ ጻፍ/ፊ::

ሀ. 

ለ. 

ሐ. 

**3.** ከዚህ በታች ለተሰጡት የድግግሞሽ ዩኒታቸውን ጻፍ/ፊ::

ሀ. 

ለ. 

ሐ. 

መ. 

4. ከዚህ በታች ከተሰጠው ሠንጠረዥ ላይ ቁልቁል ወይም ወደ ጎን በተቀቡት ቀለሞች ቅደም ተከተል የተፈጠሩትን ፓተርኖች በመፈለግ ተናገር/ሪ::



## 5.2 የጎደለ አባል

### ትግበራ 5.2

ከዚህ በታች ለተሰጡት ፓተርኖች በባዶ ቦታ ከአባላት ውስጥ የጎደለውን ሙላበት/ዪበት:: ጎደለ ያልከውን/ሽውን ለምን እንደመረጥክ/ሽ ግለፅ/ጪ::

ሀ. 1፣ 3፣ 1፣ 3፣ 1፣ ____

ለ. 4፣ 7፣ 10፣ 13፣ _____፣ _____

ሐ.  ______፣______

መ.  ______፣______

## አስተውል/ዪ

1.የጎደለ አባል ማለት በነገሮች አቀመማጥ ሁኔታ ወይም ቁጥሮች ውስጥ አንድን የጎደለ ቦታ ነገር ወይም ቁጥርን በመሙላት ፓተርን የሚያስገኝልን ነው::

2. እያንዳንዱ የፓተርን አባል ቁም ይባላል::

## ምሳሌ 3

ከዚህ በታች ለተሰጡት የጎደለውን አባል ሙላበት/ዪበት::

ሀ. 2፣ 4፣ 6፣ 8፣ 10፣ 12፣ __፣ __

ለ.  ________ ፣ ________

## መልስ

ሀ. በዚህ ፓተርን ውስጥ ተከታታይ ቁሞች በሁለት ይበላለጣሉ::

ስለዚህ 12 + 2 = 14 እና 14 + 2 = 16

የጎደሉት አባላት 14 እና 16 ናቸው::

ሙሉ ፓተርኑን ስንጽፍ 2፣ 4፣ 6፣ 8፣ 10፣ 12፣ 14 እና 16 ነው::

ለ. የሰማያዊ ምስል ፓተርን፣ አርንጓዴ እና የቢጫ በተደጋጋሚ በመከታተል ይመጣል:: ከሰማያዊው ምስል ቀጥሎ አርንጓዴ ነው:: ከአርንጓዴዉ ቀጥሎ ቢጫው ነው:: የመጀመሪያው ባዶ ቦታ  እና ሁለተኛው ደግሞ  ነው::

ስለዚህ አጠቃላይ ፓተርኑ



## መልመጃ 5.2

1. ከዚህ በታች ለተሰጡት ፓተርኖች ውስጥ የጎደሉትን ቁሞች ሙሏ/ዪ::

ሀ. 8፣ 10፣ 12፣ 14፣ 16፣ _______፣ _________

ለ. 1፣ 5፣ 9፣ 13፣ 17፣ 21፣ _______፣ _________

ሐ. 5፣ 10፣ 15፣ 20፣ 25፣ 30፣ ______፣ _______

መ. 10፣ 20፣ 30፣ _____፣ 50፣ 60፣ 70

ሠ. 22፣ 27፣ 32፣ 37፣ ___፣ 47፣ 52፣ 57

ረ. 6፣ 13፣ _____፣ 27፣ 34፣ 41፣ ___

2. ከዚህ በታች የተሰጠውን ሠንጠረዥ በቀሩት ቁሞች ሙሏ/ዪ::

| የሰው ብዛት | የእጅ ብዛት | የእጅ ጣቶች ብዛት |
|---|---|---|
| **2** | 4 | 20 |
| **4** | | 40 |
| **6** | 12 | |
| | 16 | 80 |
| **10** | | |
| | 24 | 120 |

3. ከዚህ በታች የተሰጡትን ፓተርኖች ሙሉ ለማድረግ የሚሆነውን ነገር ከሳጥኑ ውስጥ ምረጥ/ጪ::

ሀ. 

ለ. 

ሐ. 

መ. 

4. ከዚህ በታች በሠንጠረዡ ከተሰጡት ነገሮች ውስጥ በመምረጥ ባዶ ቦታዎቹን ሙላ/ዪ::



ሀ. 

ለ. 

ሐ. 

መ. 

5. ከዚህ በታች ለተሰጡት ፓተርኖች የጎደሉትን ቦታዎች ሙላ/ዪ::

ሀ. 

ለ.  ______

ሐ.  ______

መ.  ______

ሠ.  ______  ______

## በ"ኛ" ተራ ቁጥር ላይ ያለውን ቁም መፈለግ፡፡

### ምሳሌ 4

በ2፣ 7፣ 12፣ 17፣ 22፣ 27 ፓተርን ውስጥ ያሉ ቁጥሮች ስንተኛ ቁም እንደሆኑ ግለፅ/ጪ።

2- 1ኛ ቁም    17- 4ኛ ቁም    7- 2ኛ ቁም    22-5ኛ ቁም

12- 3ኛ ቁም    27- 6ኛ ቁም

### መልመጃ 5.3

1. ከዚህ በታች በተሰጡት ፓተርኖች ውስጥ እያንዳንዱ የፓተርን አባል ስንተኛ ቁም እንደሆነ ፃፍ/ፊ።

   ሀ. 10፣ 22፣ 34፣ 46፣ 58፣ 70    ለ. 100፣ 106፣112፣118፣124

2. ከዚህ በታች በተሰጡት ፓተርኖች ውስጥ 6ኛ እና 8ኛ ቁሞች ስንት ይሆናሉ?

   ሀ. 9፣ 12፣ 15፣...    ለ. 10፣ 20፣ 30፣...    ሐ. 36፣ 42፣ 48፣...

   መ. 125፣ 150፣ 175፣...

3. የ2፣ 4፣ 6፣...10ኛ ቁም ፈልግ/ጊ::

4. የ10፣ 20፣ 30፣... 12ኛ ቁም ስንት ይሆናል?

# ምዕራፍ 6




# የርዝመት መጠነቁስ እና ይዘት ስፍሮች

## 6.1 ርዝመትን በባህላዊ እና በሳንቲሜትር እና በሜትር መስፈር

### ሀ. ርዝመትን በባህላዊ መስፈር

የጥንት ሰዎች ዘመናዊ የመስፈሪያ መሳሪያዎች ከመኖራቸው በፊት የአንድን ነገር ርዝመት ለማወቅ የሰውነት አካሎቻቸውን ይጠቀሙ ነበር:: በዚህ አገር ውስጥ የባህላዊ የርዝመት መስፈሪያዎች እንደ ክንድ፣ጫማ፣ስንዝር፣እርምጃ እና ገመድ ይጠቀሙ ነበር::

### ክንድ

**ትግበራ 6.1**

1. ከአምስቱ የእጅ ጣቶች ውስጥ
   ሀ. የትኛው ረጅም ነው?
   ለ. የትኛው አጭር ነው?
2. የጠረጴዛችሁን የጎኑን ርዝመት በክንድህ/ሽ ስፈር/ሪ:: ስንት ሆነ?



## ጫማ

### ትግበራ 6.2

የክፍላችሁን ርዝመት ወይም ጎን በጫማችሁ በመስፈር ስንት እንደሆነ ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡



## ስንዝር

### ትግበራ 6.3

የጠረጴዛህን/ሽን ርዝመት በስንዝር ስትሰፍር/ሪ ምን ያህል ይሆናል?



## እርምጃ




### ትግበራ 6.4

የክፍላችሁን ጎን በእርምጃ ተራ በተራ በጫማችሁ በመስፈር ስንት እንደሆነ ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

## ገመድ

### ትግበራ 6.5

ገመድ በመጠቀም የመረብ ኳስ ሜዳ ርዝመትን ስፈር/ሪ::



## ለ. ርዝመትን በሳንቲሜትር እና በሜትር መስፈር

አንድን ነገር ለመስፈር የምንጠቀምበት ዘመናዊ የርዝመት መስፈሪያ እንደ ሜትርና ሳንቲሜትር ያሉ ናቸው:: ሳንቲሜትርን አሳጥረን ስንጽፍ "ሳ.ሜ" ብለን እንጽፋለን:: ሜትርን ደግሞ አሳጥረን ስንጽፍ "ሜ" ብለን እንጽፋለን::

### ትግበራ 6.6

1. ማስመሪያን በመጠቀም ከዚህ በታች የተሰጡትን ነገሮች ርዝመታቸውን ስፈር/ሪ::
   ሀ. የደብተር ርዝመት　　　ለ. የሒሳብ መጽሐፍ ርዝመት
2. ሜትርን በመጠቀም ከዚህ በታች የተሰጡትን ነገሮች ርዝመታቸውን ስፈር/ሪ::
   ሀ. የጠረጴዛ ርዝመት　　　ለ. የመማሪያ ክፍል ርዝመት

**አስተውል/ይ**

**1ሜ = 100ሳ.ሜ**

**ምሳሌ 1**

ከዚህ በታች የተሰጡትን ባዶ ቦታዎች ትክክለኛ በሆነ መልስ ሙላ/ዪ::

ሀ. 3ሜ = _________ ሳ.ሜ　　　ለ. 5ሜ =__________ሳ.ሜ

ሐ. 200ሳ.ሜ =______ ሜ　　　መ. 600ሳ.ሜ =________ሜ

**መልስ**

| | |
|---|---|
| **ሀ.** 3ሜ = ________ ሳ.ሜ ይሆናል::<br>1ሜ = 100 ሳ.ሜ<br>ስለዚህ<br>3ሜ=3 ×100ሳ.ሜ = 300ሳ.ሜ ይሆናል:: | **ለ.** 5ሜ = ________ ሳ.ሜ ይሆናል::<br>1ሜ = 100 ሳ.ሜ<br>ስለዚህ<br>5ሜ=5 ×100ሳ.ሜ =500ሳ.ሜ ይሆናል:: |
| **ሐ.** 200ሳ.ሜ =______<br>1ሜ = 100ሳ.ሜ<br>200ሳ.ሜ = 2ሜ ይሆናል:: | **መ.** 600ሳ.ሜ =________<br>1ሜ = 100ሳ.ሜ<br>600ሳሜ = 6ሜ ይሆናል:: |



**መልመጃ 6.1**

1. ከዚህ በታች የተሰጡትን ባዶ ቦታዎች ትክክለኛ በሆነ መልስ ሙላ/ዪ::

   ሀ. 7ሜ = __________ ሳ.ሜ

   ለ. 8ሜ = __________ ሳሜ

   ሐ. 10ሜ = __________ ሳ.ሜ

   መ. 100 ሳ.ሜ = ______ ሜ

   ሠ. 400ሳ.ሜ = __________ ሜ

   ረ. 900 ሳ.ሜ = ______ ሜ

2. በሁለት ክፍሎች መካከል ያለው ርዝመት 4ሜ ነው:: በክፍሎቹ መካከል ያለው ርዝመት በሳንቲሜትር ምን ያህል ይሆናል?
3. 800 ሳ.ሜ የሚረዝም ገመድ ርዝመቱ በሜትር ሲገለጽ ምን ያህል ይሆናል?

## 6.2 ተመሳሳይ የርዝመት ዩኒቶችን መደመር እና መቀነስ

**ትግበራ 6.7**

1. 7ሜ የሚረዝም ገመድ ካለህና ሌላ 5ሜ የሚረዝም ገመድ ቢጨመርልህ/ሽ በአጠቃላይ ስንት ሜትር የሚረዝም ገመድ ይኖረሃል/ሪሻል?
2. 10 ሳ.ሜ እና 8ሳ.ሜ አንድ ላይ ስንት ሳ.ሜ ነው?

3. 70 ሳ.ሜ ከሚረዝም እንጨት ላይ 20ሳ.ሜ የሚረዝም እንጨት ከቆረጥክ/ሽ ምን ያህል ይቀራል?

## ምሳሌ 2

ለሊሴ የቤታቸውን ጠረጴዛ ርዝመት በሜትር ስትሰፍር 3ሜ ሆነ:: ሰንበቶ ደግሞ ሌላ የቤታቸውን ጠረጴዛ ርዝመት ሲሰፍር 2ሜ ሆነ:: የሁለቱ ጠረጴዛዎች ርዝመት በአጠቃላይ ስንት ነው?




የለሊሴ የጠረጴዛ ርዝመት 3ሜ        የሰንበቶ የጠረጴዛ ርዝመት 2ሜ

## መልስ

የሁለቱ ጠረጴዛዎች ድምር 3ሜ + 2ሜ = 5ሜ ነው::

## ምሳሌ 3

ከዚህ በታች የተሰጡትን በተቀመጠው አሃድ ደምር/ሪ::

ሀ. 2ሜ + 5ሜ = ______   ለ. 12 ሳ.ሜ + 5ሳ.ሜ = ____   ሐ. 54ሜ + 13ሜ = _____

መ. 95ሜ+ 5ሜ = _____   ሠ. 78ሳ.ሜ + 7ሳ.ሜ = ______

## መልስ

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. 2ሜ + 5ሜ = 7ሜ | ለ. 12ሳ.ሜ+5ሳ.ሜ = 17ሳ.ሜ | ሐ. 54ሜ + 13ሜ = 67ሜ |
| መ. 95ሜ + 5ሜ =100ሜ | ሠ. 78ሳ.ሜ+7ሳ.ሜ= 85 ሳ.ሜ | |

## ምሳሌ 4

ከዚህ በታች የተሰጡትን አቀናንስ::

ሀ. 9ሜ – 5ሜ = ______   ለ. 27ሳ.ሜ – 6ሳ.ሜ = ______   ሐ. 54ሜ – 13ሜ =__

መ. 98ሜ – 4ሜ = ______   ሠ. 63ሳ.ሜ – 2ሳ.ሜ = ______

## መልስ

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. 9ሜ – 5ሜ = 4ሜ | ለ. 27ሳ.ሜ – 6ሳ.ሜ= 21ሳ.ሜ | ሐ. 54ሜ – 13ሜ = 41ሜ |
| መ. 98ሜ – 4ሜ= 94ሜ | ሠ. 63ሳ.ሜ –2ሳ.ሜ= 61ሳ.ሜ | |

## ምሳሌ 5

ሐዊ በ1ሰዓት ውስጥ 300ሜ ርቀት ብስክሌት በመንዳት ተለማመደች:: በ3ሰዓት ውስጥ በተመሳሳይ የብስክሌት ልምምድ ምን ያህል ርቀት በሜትር ትለማመዳለች?



## መፍትሔ

ሐዊ በ1ሰዓት ውስጥ 300ሜ ርቀት ብስክሌት መንዳት ተለማመደች:: በ3ሰዓት ውስጥ ተመሳሳይ የብስክሌት ልምምድ ርቀት በሜትር ማድረግ የምትችለው 300ሜ + 300ሜ + 300ሜ = 900ሜ ይሆናል::

## ምሳሌ 6

90ሳ.ሜ ከሚረዝም ሽቦ ላይ 30ሳ.ሜ የሚረዝም ሽቦ ከተቆረጠ የሚቀረው ሽቦ ምን ያህል ይረዝማል?

## መፍትሔ

የመጀመሪያው ሽቦ ርዝመት 90ሳ.ሜ ነው::

የሚቀነሰው ርዝመት 30ሳ.ሜ ነው::

ከተቀናሹ ሽቦ በኃላ የምታገኘው/ኚው ርዝመት 90ሳ.ሜ – 30ሳ.ሜ = 60ሳ.ሜ ይሆናል::

## መልመጃ 6.2

1. ከዚህ በታች የተሰጡትን ባዶ ቦታ በትክክለኛ መልስ ሙላ/ዪ::

ሀ. 13ሳ.ሜ + 15ሳ.ሜ = _______ሳ.ሜ   ለ. 33ሳ.ሜ + 28ሳ.ሜ = ______ሳ.ሜ

ሐ. 51ሜ + 2ሜ = ________ሜ   መ. 84ሳ.ሜ + 7ሳ.ሜ = _______ሳ.ሜ

ሠ. 38ሳ.ሜ – 26ሳ.ሜ = _______ ሳ.ሜ　　ረ. 97ሜ – 45ሜ = _________ሜ

2. ከዚህ በታች የተሰጡትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ መልስ ሙላ/ዪ::

ሀ. 29 ሳ.ሜ + _____ሳ.ሜ = 49ሳ.ሜ　　ለ. _____ + 15ሜ = 48ሜ

ሐ. 72 ሳ.ሜ + ____ ሳ.ሜ = 88ሳ.ሜ　　መ. 39 ሳ.ሜ + _____ ሳ.ሜ = 69 ሳ.ሜ

3. ደራርቱ 160 ሳ.ሜ የሚረዝም ሲንቄ ትይዛለች:: አያንቱ ደግሞ 170 ሳ.ሜ የሚረዝም ሲንቄ ትይዛለች::

ሀ. ደራርቱ እና አያንቱ የሚይዙት ሲንቄዎች ርዝመት በአንድ ላይ በሳ.ሜ ስንት ነዉ ?

ለ. አያንቱ የምትይዘው ሲንቄ ደራርቱ ከምትይዘው ሲንቄ በምን ያህል ይረዝማል?

## 6.3 መጠነቁስን በግራም እና በኪሎግራም መስፈር

### ትግበራ 6.8




1. መጠነቁስን በምን መስፈር ተችላለህ?

2. መጠነቁስህ/ሽ በኪሎግራም ምን ያህል ነው?

**አስተውል/ይ**

መጠነቁስን ለመስፈር የሚረዱ እንደ ግራም እና ኪሎግራም ናቸው::

ግራምን (ግ) ሲወክል የኪሎግራም ተወካይ ደግሞ (ኪ.ግ) ይወከላል::

1ኪ.ግ = 1000ግ

የነገሮችን መጠነቁስ የምንሰፍርበት የባህላዊ መስፈሪያዎች እንደ ቁና፣ስልቻ፣ቅል እና የመሳሰሉት ናቸው::

## ምሳሌ 7

ከዚህ በታች የተሰጡትን ፈልግ::

1. 4 ቅል ገብስ እና 6 ቅል ገብስ አንድ ላይ ስንት ቅል ገብስ ነው?
2. 20 ቁና ጤፍ እና 30 ቁና ጤፍ አንድ ላይ ስንት ቁና ጤፍ ነው?
3. 25 ስልቻ ኑግ እና 50 ስልቻ ኑግ አንድ ላይ ስንት ስልቻ ኑግ ነው?
4. ፉፉ 70 ስልቻ ገብስ ካመረተው ላይ 10 ስልቻ ገብስ ለድሆች ሰጠ:: ለፉፉ ስንት ስልቻ ገብስ ቀረለት?

## መፍትሔ

1. 4 ቅል ገብስ + 6 ቅል ገብስ = 10 ቅል ገብስ ነው::
2. 20 ቁና ጤፍ + 30 ቁና ጤፍ = 50 ቁና ጤፍ ነው::
3. 25 ስልቻ ኑግ + 50 ስልቻ ኑግ = 75 ስልቻ ኑግ ነው::
4. ፉፉ 70 ስልቻ ገብስ ምርት አምርቷል::

   ፉፉ ለድሃዎች 10 ስልቻ ገብስ ሰጥቷል::

   ለፉፉ የቀረለትን ገብስ ለማግኘት ካመረተው የስልቻ ገብስ ላይ ለድሃዎች የሰጠውን የስልቻ ገብስ መቀነስ ነው::

   ይህም 70–10 =60 ስልቻ ነው::

## መልመጃ 6.3

1. ከዚህ በታች የተሰጡትን ፈልግ::

   ሀ. መርጋ 10 ቁና ስንዴ እና 20 ቁና ጤፍ ወደ ወፍጮ ቤት ወስዶ አስፈጨ:: መርጋ አንድ ላይ ምን ያህል እህል አስፈጨ?

   ለ. ኦብሴ ካመረተችው 50 ስልቻ ቦቆሎ ውስጥ 10 ስልቻ ቦቆሎ ገበያ ወስዳ ሸጠች:: ለኦብሴ ስንት ስልቻ ቦቆሎ ቤት ውስጥ ይቀርላታል?

2. ጋዲሴ 2ኪ.ግ ሙዝ ገዛች:: ኩለኒ ደግሞ 1ኪ.ግ ደግሞ ሙዝ ገዛች:: ከጋዲሴ እና ከኩለኒ ብዙ ኪሎግራም የገዛው ማነው?

3. ገመቹ እና ቶላ በአጠቃላይ 40ኪ.ግ እህል ተሸክመው ወደ ወፍጮ ቤት ሄዱ:: ቶላ ብቻውን 21ኪ.ግ ተሸከመ:: በይበልጥ የተሸከመዉ ቶላ ወይስ ገመቹ ነው?

4. ከዚህ በታች የተሰጡትን ነገሮች መጠነቁሳቸውን ለመስፈር ተመራጭ የመጠነቁስ ዩኒት የሆነውን ጻፍ/ፊ::

ሀ. የጣት ቀለበት ለ. የአንገት ወርቅ ሐ. ስኳር መ. ጤፍ

## 6.4 ተመሳሳይ ዩኒት ያላቸውን መጠነቁሶች መደመር እና መቀነስ

### ትግበራ 6.9

የሁለት ተማሪዎችን መጠነ-ቁስ ጠይቃቸው/ቂያቸው:: መጠነ-ቁሳቸው ምን ያህል እንደሚበላለጥ በኪሎግራም ግለጽ/ጪ::

### ምሳሌ 9

አቶ አብዲ ለበቤተሰቡ 2 ኪሎግራም ብርቱካን እና 2 ኪሎግራም ሎሚ ገዛ:: አቶ አብዲ በአጠቃላይ ስንት ኪሎግራም ፍራፍሬዎችን ለቤተሰቡ ገዛ?

| | |
|---|---|
|  |  |
| 2 ኪ.ግ ብርቱካን | 2 ኪ.ግሎሚ |

**መልስ**: 2 ኪ.ግ ብርቱካን + 2 ኪ.ግ ሎሚ= 4 ኪ.ግ አትክልት

### ምሳሌ 10

ከዚህ በታች የተሰጡትን ባዶ ቦታ ሙላ/ይ::

ሀ. 2ግ + 5ግ =_____ ለ. 8ኪ.ግ + 4ኪ.ግ =_______

ሐ. 14ግ + 9ግ =______ መ. 18ኪ.ግ + 21ኪ.ግ =_______

**መልስ**

| | |
|---|---|
| ሀ. 2ግ + 5ግ = 7ግ | ለ. 8ኪ.ግ + 4ኪ.ግ = 12ኪ.ግ |
| ሐ. 14ግ + 9ግ = 23ግ | መ. 18ኪ.ግ + 21ኪ.ግ = 39ኪ.ግ |

## ምሳሌ 11

ከዚህ በታች የተሰጡትን ባዶ ቦታ ሙላ/ይ::

ሀ. 8ግ – 2ግ = ______ ለ.13ግ – 3ግ = _____

ሐ. 27ኪ.ግ – 5ኪ.ግ = _____ መ. 36ኪ.ግ – 25ኪ.ግ = _____

**መልስ**

| | |
|---|---|
| ሀ. 8ግ – 2ግ = 6ግ | ለ. 13ግ – 3ግ = 10ግ |
| ሐ. 27ኪ.ግ – 5ኪ.ግ = 22ኪ.ግ | መ. 36 ኪ.ግ – 25ኪ.ግ = 11ኪ.ግ |

## መልመጃ 6.4

1. ከዚህ በታች የተሰጡትን ደምር/ሪ::

   ሀ. 7ኪ.ግ + 8 ኪ.ግ = ____________ ለ. 38ኪ.ግ + 29ኪ.ግ =________

   ሐ. 48ኪ.ግ + 45ኪ.ግ = __________ መ. 20ግ + 50ግ = ____________

   ሠ. 47ኪ.ግ + 34ኪ.ግ = _________ ረ. 81ኪ.ግ + 19ኪ.ግ = _______

2. ከዚህ በታች የተሰጡትን ቀንስ/ሺ::

   ሀ. 6ኪ.ግ – 4ኪ.ግ = ____________ ለ. 17ግ – 9ግ = ______________

   ሐ. 88ኪ.ግ – 39ኪ.ግ = ________ መ. 52ኪ.ግ – 41ኪ.ግ = _______

   ሠ. 86ኪ.ግ – 79ኪ.ግ = _________ ረ. 63ኪ.ግ – 15ኪ.ግ = _________

3. ወ/ሮ ጃለኔ ገበያ ሄዳ 25ኪ.ግ ስንዴ፣ 56ኪ.ግ ጤፍ እና 23ኪ.ግ ቦቆሎ ገዙ::
   ወ/ሮ ጃለኔ

   ሀ. ቦቆሎ እና ስንዴ በአጠቃላይ ምን ያህል ገዛች?

   ለ. ጤፍ እና ስንዴ በአጠቃላይ ምን ያህል ገዛች?

   ሐ. ጤፍ እና ቦቆሎ በአጠቃላይ ምን ያህል ገዛች?

4. መገርቱ እና ልጇ 69 ኪ.ግ መጠነቁስ አላቸው::ልጇ ብቻውን 3ኪ.ግ መጠነቁስ አለው:: መገርቱ መጠነቁሷ ምን ያህል ነው?

# 6.5 የፈሳሽ ይዘትን በሚሊ ሊትር እና በሊትር መስፈር

## ትግበራ 6.10

1. አንድ ሙሉ ብርጭቆ ውሃ በመስፈር ወደ ጆግ ገልብጥ/ጪ:: ስንቱ ብርጭቆ ጆጉን ይሞላል?



2. በቀን ስንት ሊትር ውሃ ትጠጣለህ/ሽ?

የጥንት ሰዎች ዘመናዊ የይዘት መስፈሪያ ከመምጣታቸው በፊት እንደ ማሰሮ፣ጋን፣ጽዋ፣ዋንጫ፣እንስራ እና የመሳሰሉትን ይጠቀሙ ነበር::

### ምሳሌ 12

ጉታ በየቀኑ 3 ጀሪካን ውሃ ይቀዳል:: በአራት ቀን ውስጥ ስንት ጀሪካን ይቀዳል?

**መፍትሔ**

ጉታ በየቀኑ 3 ጀሪካን ውሃ ይቀዳል::

በ4 ቀን ውስጥ ደግሞ $4 \times 3$ ጀሪካን ውሃ $= 12$ ጀሪካን ውሃ ይቀዳል::

### ምሳሌ 13

ጫልቱ 2 ጠርሙስ የጣዝማ ማር ገዛች:: መገርቱ ደግሞ 3 ጠርሙስ የጣዝማ ማር ገዛች:: በአጠቃላይ ጫልቱ እና መገርቱ ስንት ጠርሙስ የጣዝማ ማር ገዙ?

**መፍትሔ** ጫልቱ 2 ጠርሙስ የጣዝማ ማር እናመገርቱ ደግሞ 3 ጠርሙስ የጣዝማ ማር ገዙ:: በአጠቃላይ ሁለቱ የገዙት የጣዝማ ማር $2 + 3 = 5$ ነው::

## ምሳሌ 14

**አቶ ባጫ አምስት የቤተሰብ አባላት አለው:: በየቀኑ ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ሁለት ሲኒ ወተት ቢያስፈልገው በአንድ ሳምንት ውስጥ በአጠቃላይ ስንት ሲኒ ወተት ያስፈልጋቸዋል?**

## መፍትሔ

አቶ ባጫ አምስት የቤተሰብ አባላት አለው:: በየቀኑ ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ሁለት 2 ሲኒ ወተት ያስፈልገዋል:: በአንድ ቀን ውስጥ $5\times 2 = 10$ ሲኒ ወተት ያስፈልጋል: : በአንድ ሳምንት ውስጥ ለአቶ ባጫ ቤተሰብ $10 \times 7 = 70$ ሲኒ ወተት ያስፈልጋቸዋል::

**ሚሊሊትር እና ሊትር** ዘመናዊ የፈሳሽ ይዘት ዩኒት ናቸው::

አነስተኛ ይዘት ያላቸውን ፈሳሾችን ለመስፈር ሚሊሊትር(ሚ.ሊ) እንጠቀማለን::

ትልቅ ይዘት ያላቸውን ፈሳሾችን ለመስፈር ሊትር(ሊ) እንጠቀማለን:: ፈሳሾች እንደ **ውሃ፣ ዘይት፣ ወተት፣ የተለያዩ ነዳጅ፣ ጠጅ** እና ወዘተ ናቸው::

**አስተውል/ዩ**. የፈሳሾች ይዘት ዩኒት ሊትር ይባላል::

ሊትር በአጭሩ (ሊ) ተብሎ ይጻፋል::

1ሊ = 1000ሚሊ

## መልመጃ 6.5

1. ገላኔ እና ጉዲና የመማሪያ ክፍላቸውን ለማጽዳት ውሃ ቀዱ:: ገላኔ 2 ሊትር ከቀዳች እና ጉዲና ደግሞ 3 ሊትር ከቀዳ አነስተኛ ሊትር የቀዳው ማነው?
2. ወ/ሮ ገመዴ 4 ሰዎችን ሶስት ሶስት ዋንጫ ጠላ ጋበዘቻቸው:: ወ/ሮ ገመዴ በአጠቃላይ ስንት ዋንጫ ጠላ ጋበዘቻቸው?
3. ቤተሰቦችህ ውሃ የሚቀዱበትን ዕቃዎች ጻፍ/ፊ::

# 6.6 ተመሳሳይ ዩኒት ያላቸውን ይዘቶች መደመር እና መቀነስ

## ምሳሌ 15

ገዳ 300 ሚሊሊትር ወተት ከብርጭቆ ውስጥ ወደ ባልዲ ገለበጠ እንዲሁም 500ሚ.ሊ ሊትር ወተት ከጆግ ወደ ባልዲው ገለበጠ:: በአጠቃላይ ገዳ ስንት ሚሊሊትር ወተት ወደ ባልዲው ገለበጠ?

## መፍትሔ

|  |  |  |
|---|---|---|
| **ብርጭቆ** | **ጆግ** | **ባልዲ** |
| 300ሚ.ሊ. + | 500ሚ.ሊ. = | 800ሚ.ሊ. |

## ምሳሌ 16

ከዚህ በታች በተሰጡት ዩኒቶች ላይ በመመስረት ደምር/ሪ::

**ሀ.** 5ሊ. + 2ሊ. = ____ **ለ.** 59ሚ.ሊ. + 30ሚ.ሊ. = ____ **ሐ.** 43ሚ.ሊ. + 75ሚ.ሊ. = ___

## መፍትሔ

**ሀ.** 5ሊ. + 2ሊ. = _____

ይሄንን ለመፈለግ በመጀመሪያ 5 እና 2ን እንደምራለን:: በመቀጠል ዩኒትን ከጎኑ እናስቀምጣለን:: ይህም 5ሊ. + 2ሊ. = 7ሊ.

**ለ.** 59ሚ.ሊ. + 30ሚ.ሊ. = _____

ይሄንን ለመፈለግ በመጀመሪያ 59 እና 30 እንደምራለን:: በመቀጠል ዩኒቱን ከጎኑ እናስቀምጣለን:: ይህም 59ሚ.ሊ. + 30ሚ.ሊ. = 89ሚ.ሊ. ነው::

ሐ. 43ሚ.ሊ + 75ሚ.ሊ= _____

በመጀመሪያ 43 እና 75ን እንደምራለን:: በመቀጠል ዩኒቱን ከጎኑ እናስቀምጣለን::

ይህም 43ሚ.ሊ + 75ሚ.ሊ = 118ሚ.ሊ ነው::

## ምሳሌ 17

ከዚህ በታች በተሰጡት ዩኒቶች ላይ በመመስረት ቀንስ/ሽ::

ሀ. 8ሊ – 3ሊ =_____ ለ. 19ሚ.ሊ – 7ሚ.ሊ = _____ ሐ. 34ሚ.ሊ – 27ሚ.ሊ =_____

### መፍትሔ

ሀ. 8ሊ – 3ሊ =____

በመጀመሪያ 3ን ከ8 ላይ እንቀንሳለን:: በመቀጠል በመቀጠል ዩኒትን ከጎኑ እናስቀምጣለን:: ይህም 8ሊ – 3ሊ= 5ሊ ነው::

ለ. 19ሚ.ሊ – 7ሚ.ሊ = _____

በመጀመሪያ 7ን ከ19 ላይ እንቀንሳለን:: በመቀጠል ዩኒትን ከጎኑ እናስቀምጣለን:: ይህም 19ሚ.ሊ – 7ሚ.ሊ= 12ሚ.ሊ ነው::

ሐ. 34ሚ.ሊ – 27ሚ.ሊ =_____

በመጀመሪያ 27ን ከ34 ላይ እንቀንሳለን:: በመቀጠል ዩኒትን ከጎኑ እናስቀምጣለን:: ይህም 34ሚ.ሊ – 27ሚ.ሊ= 7ሚ.ሊ ነው::

## ምሳሌ 18

አቶ ለታ በቀን ለመኪናው 15ሊትር ነዳጅ ይጠቀማል:: አቶ ለታ ለ3 ቀናት ቢጓዝ ምን ያህል ሊትር ነዳጅ ያስፈልገዋል?

### መፍትሔ

በቀን ለመኪናው 15ሊትር ነዳጅ ይጠቀማል::

በ3 ቀን ውስጥ 15ሊ + 15 ሊ+ 15ሊ = 45 ሊትር ይጠቀማል::

## መልመጃ 6.6

1. ከዚህ በታች በተሰጡት ዩኒቶች ላይ በመመስረት ደምር/ሪ::

ሀ. 54ሊ+ 24ሊ = _____ ለ. 89ሚ.ሊ + 11ሚ.ሊ = _____

ሐ. 67ሊ+ 31ሊ = _____ መ. 38ሚ.ሊ + 49ሚ.ሊ = _____

2. ከዚህ በታች በተሰጡት ዩኒቶች ላይ በመመስረት ቀንስ/ሺ::

ሀ. 26ሊ – 5ሊ =_____

ለ. 87ሚ.ሊ – 19ሚ.ሊ = _____

ሐ. 75ሊ – 14ሊ =_____

መ. 34ሊ– 15ሊ =_____

3. ጫልቱ ሰኞ 17 ሊትር ወተት፣ ማክሰኞ 24 ሊትር ወተት እና ሮብ 19 ሊትር ወተት ሸጠች:: በአጠቃላይ ጫልቱ ስንት ሊትር ወተት ሸጠች?

4. አንዲት ላም በቀን 4 ሊትር ወተት ከታለበች በ20 ቀን ውስጥ ስንት ሊትር ወተት ትታለባለች?

# ምዕራፍ 7




# የዳታ አያያዝ

## 7.1 ዳታ መሰብሰብ

### ትግበራ 7.1

1. ቤተሰቦችህ/ሽ ስንት ልጆች አላቸው?
2. ስንት እህቶች አለህ/ሊሽ?
3. ስንት ወንድሞች አለህ/ሊሽ?
4. የክፍልህ/ሽ ተማሪዎች ብዛት ስንት ናቸዉ?

   የወንዶች እና የሴቶችን ብዛት ለይ/ዪ።

### ምሳሌ 1

የአቶ ጉረሙ እና የአቶ ሞቲ ቤተሰብ ጥጆች፣ ላሞች፣ በሬዎች እና በጎች እንደሚከተለው በምስል ቀርበዋል።

ሀ. የአቶ ጉርሙ ላሞች እና በሬዎች ብዛት ስንት ይሆናሉ?

ለ. የአቶ ጉረሙ እና የአቶ ሞቲ በጎች አንድ ላይ ስንት ናቸው።

| የአቶ ጉርሙ ከብቶች | የአቶ ሞቲ ከብቶች |
|---|---|




## መፍትሔ

**ሀ.** የአቶ ጉርሙ ላሞች ብዛት 3 ናቸው።

የአቶ ጉርሙ በሬዎች ብዛት 3 ናቸው።

በአጠቃላይ የአቶ ጉርሙ ላሞች እና በሬዎች ብዛት $3 + 3 = 6$

**ለ.** የአቶ ጉርሙ በጎች ብዛት 4.

የአቶ ሞቲ በጎች ብዛት 3 ናቸው።

በአጠቃላይ የአቶ ጉርሙ በጎች እና የአቶ ሞቲ በጎች ብዛት $4 + 3 = 7$

## አስተውል/ዪ

የሚከተለው ሠንጠረዥ የጭረት/የታሊ ምልክትን በቁጥር ያሳያል

| በጭረት/ታሊ | / | // | /// | //// | ~~////~~ |
|---|---|---|---|---|---|
| በቁጥር | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |

## ምሳሌ 2

**ከዚህ በታች ያሉትን ፍራፍሬዎች ብዛታቸውን በጭረት እና በቁጥር ግለጽ/ጪ።**



### መፍትሔ

| የፍራፍሬ አይነት | ጭረት | በቁጥር |
|---|---|---|
|  አፕል | 𝍸 | 5 |
|  አናናስ | //// | 4 |
|  ብርቱካን | /// | 3 |
|  ሙዝ | /// | 3 |

## ምሳሌ 3

ከዚህ በታች ያሉትን ምስል ብዛት እያንዳንዳቸውን በጭረት እና በቁጥር አስቀምጥ/ጪ።



### መፍትሔ

| የምስል አይነት |  |  |  |  |  |  |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ጭረት | ~~////~~ | /// | //// | /// | /// | // |
| ቁጥር | 5 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 |

## መልመጃ 7.1

1. ናቤክ የአብዲ ቦሩ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሁለተኛ ክፍል ተማሪ ነው። ናቤክ በሰኔ ወር ውስጥ ከሰኞ እስከ አርብ እንደሚከተለው ችግኝ ተከለ። ይህን ዳታ በጭረት እና በቁጥር በመቁጠር ጻፍ/ፊ።

| ቀን | የችግኝ ምስል | ጭረት | ቁጥር |
|---|---|---|---|
| ሰኞ |  | | |
| ማክሰኞ |  | | |
| ሮብ |  | | |
| ሀሙስ |  | | |
| አርብ |  | | |

2. ኢፍቱ ጎበዝ ተማሪ ነች ። በሂሳብ፣ በገዳ፣ በእንግሊዝኛ፣ በኦሮሚኛ እና በአከባቢ ሳይንስ የትምህርት አይነቶች ከ10 ውስጥ ተፈትና 10፣ 9፣ 7፣ 9 እና 8 በቅደም ተከተል አስመዝግባለች።

ሀ. ኢፍቱ በየትኛው የትምህርት አይነት ከፍተኛ ነጥብ አመጣች?

ለ. ኢፍቱ በየትኛው የትምህርት አይነት ዝቅተኛ ነጥብ አመጣች?

## 7.2 ከስዕላዊ ግራፎች ላይ ዳታን መመደብ

### ትግበራ 7.2

ከክፍላችሁ ተማሪዎች ውስጥ ስማቸውን የምታውቀውን/ቂውን ጻፍ/ፊ።

15 ተማሪዎች የሚከተለውን ፍራፍሬ ከገዙ እና እያንዳንዳቸው 1 ፍራፍሬ ብቻ ከገዙ ይህን መረጃ በግራፍ አሳይ/ዪ።



| የፍራፍሬ አይነት | የፍራፍሬዎች ብዛት |
|---|---|
| አፕል |  |
| ሙዝ |  |
| አናናስ |  |
| ብርቱካን |  |

## ምሳሌ 5

ከዚህ በታች ከተሰጡት ምስሎች እንደምትመለከቱት አቶ ጫላ 4 አውራ ዶሮዎች፣ 5 ላሞች፣ 3 ግመሎች፣ 2 አህዮች፣ 2 ውሾች እና 2 ጥንቸሎች አለው። ይህን መረጃ በግራፍ አሳይ/ዪ።





## ምሳሌ 6

የሚከተሉትን ምስሎች በግራፍ መድብ።






## መልመጃ 7.2

የሚከተሉትን ቅርጾች በግራፍ መድብ/ቢ።



# 7.3 ነገሮችን በመጠቀም ዳታን ማቀናጀት

## ምሳሌ 7

የተሰጠውን የግራፍ ምስል በመጠቀም የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሺ፡፡




ሀ. ስንት ማንጎ አለ?

ለ. ስንት ሙዝ አለ?

ሐ. ስንት አፕል አለ?

መ. ስንት ብርቱካን አለ?

**መፍትሔ**

ሀ. 6 ማንጎዎች አሉ።

ለ. 5 ሙዞች አሉ።

ሐ. 4 አፕሎች አሉ።

መ. 4 ብርቱካኖች አሉ።

## መልመጃ 7.3

ከዚህ በታች የተሰጠው ግራፍ የልጆችን የፍራፍሬ መመገብ ፍላጎትን ያሳያል።

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ግራፉን በመጠቀም መልስ/ሺ።




ሀ. ልጆቹ በጣም የሚወዱት ፍራፍሬ የትኛውን ነው?

ለ. ማንጎ እና አፕል የሚወዱ ልጆች ብዛት ስንት ው?

ሐ. ብርቱካን የሚወዱ ልጆች ብዛት ስንት ነው?

መ. ሙዝ እና ማንጎ የሚወዱ ልጆች ብዛት ስንት ናቸው?

# ምዕራፍ 8



# የጂኦሜትሪ ቅርጾች

## 8.1 ባለሁለት ዲያሜንሽን ቅርጾችን መመደብ እና በሀሳብ ማሳየት

### ትግበራ 8.1

1. በመማሪያ ክፍላችሁ ውስጥ ከሚገኙ ነገሮች ተመሳሳይ ቅርጽ ያላቸውን በቡድን ተወያዩበት::
2. አንድ ወረቀት ወስዳችሁ የቻላችሁን ያህል በተለያዩ ቅርጾች እጠፉት:: የሰራችሁትን ለቡድን አባላት በማሳየት ያገኛችሁትን የተለያዩ የቅርጾች አይነት እና ብዛታቸውን ተናገሩ::

### መልመጃ 8.1

1. ከዚህ በታች የተሰጡት ምስሎችን ጎናቸው ላይ በመመስረት መድብ/ቢ::



2. ከዚህ በታች የተሰጠውን ምስል ለመስራት የሚረዱት ቅርጾችን እና ብዛታቸውን ተናገር/ሪ::



| ቅርጽ |  |  |  |  |  |
|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | | | | | |

## 8.2 ቅርጾችን በጎኖቻቸው እና በነቁጦቻቸው መግለጽ

### ትግበራ 8.2

1. ደብተር፣ መጽሐፍ፣ ጠረጴዛ እና ማስመሪያ ጎን አላቸው? ነቁጥስ አላቸው? አላቸው ካላችሁ አንዳችሁ ለአንዳችሁ አሳዩ::
2. ከደብተርህ/ሽ ውስጥ አንድ ወረቀት ከቆረጥክ/ሽ ስንት ጎኖችን ታገኛለህ/ሽ?

### አስተውል/ዪ

ጎንና ነቁጥ ከዚህ በታች ባለው ምስል ላይ ተመልክቷል::




### መልመጃ 8.2

1. ከዚህ በታች ለተሰጡት ቅርጾች የጎናቸውን ብዛት እና የነቁጦቻቸውን ብዛት ሙሉ::

| ቅርጽ | የጎን ብዛት | የነቁጥ ብዛት |
|---|---|---|
|  | | |
|  | | |
|  | | |
|  | | |
|  | | |

2. ከዚህ በታች የተሰጡት ቅርጾች ባላቸው የጎን ብዛት ላይ በመመስረት ስማቸውን ሰይም/ሚ::

ሀ.  ለ.  ሐ.  መ. 

ሠ.  ረ.  ሰ.  ሸ. 

# 8.3 ተመሳሳይ ምስሎችን በመጠናቸው ማነጻጸር

## ትግበራ 8.3

ሶስቱን ጠረጴዛዎች በመጠናቸው ስታነጻጽር/ሪ

ሀ. ከሶስቱ ጠረጴዛዎች ትልቁ የቱ ነው?

ለ. ከሶስቱ ጠረጴዛዎች ትንሹ የቱ ነው?

|  |  |  |
|---|---|---|
| ሀ | ለ | ሐ |

## መልመጃ 8.3

1. ከዚህ በታች ከተሰጡት ጥንድ ጥንድ ምስሎች ከእያንዳንዳቸው ትልቁ የትኛው ነው?




2. ከዚህ በታች የተሰጡትን ምስሎች በመጠናቸው መሰረት ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተል አስቀምጥ/ጪ::










3. ከዚህ በታች ከተሰጡት ምስሎች የሚመሳሰሉትን አንድ ላይ በማምጣት ከትንሽ ወደ ትልቀ በቀደም ተከተል አስቀምጥ/ጪ::




## 8.4 ጠጣር ምስሎችን መለየት

ከጠጣር ምስሎች ጋር መተዋወቅ


ኩብ


ሬክታንግላዊ ፕሪዝም


ሲሊንደር


ኮን


ስፍር

## ትግበራ 8.4

በአከባቢህ/ሽ ከሚገኙ ነገሮች ውስጥ ከዚህ በታች ከተሰጡት ጠጣር ምስሎች ጋር የሚመሳሰሉትን ጻፍ/ፊ::

| ተ.ቁ | ጠጣር ምስሎች | የተጠቀሱት ጠጣር ምስሎች ምሳሌ |
|---|---|---|
| 1 | ሬክታንግላዊ ፕሪዝም | |
| 2 | ሉል | |
| 3 | ኩብ | |
| 4 | ሲሊንደር | |
| 5 | ኮን | |

## መልመጃ 8.4

1. ከዚህ በታች በተሰጠው ሠንጠረዥ ውስጥ በቀኝ በኩል ከተሰጡት ጠጣር ምስሎች መካከል በስተግራ የተሰጠውን ጠጣር ምስል የሚመስል አክብበት/ቢበት::

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. |  ሬክታንግላዊ ፕሪዝም |  |
| ለ. |  ሉል |  |
| ሐ. |  ሲሊንደር |  |
| መ. |  ኩብ |  |
| ሠ. |  ኮን |  |

2. ከዚህ በታች በሆሂያት ካሉ ጠጣር ምስሎች ጋር የሚመሳሰሉትን መርጠህ ባዶ ቦታው ላይ ጻፍ/ፊ::

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሀ.  | ለ.  | ሐ.  | መ.  | ሠ.  |
| ረ.  | ሰ.  | ሸ.  | ቀ.  | በ.  |
| ተ.  | ቸ.  | ኀ.  | ነ.  | ኘ.  |

ኩብ ___________________________________

ኮን___________________________________

ሉል_________________________________

ሲሊንደር ___________________________________

ሬክታንግላዊ ፕሪዝም_____________________

# ምዕራፍ 9





# የኢትዮጵያ ገንዘብ ምንዛሬ

## 9.1 የኢትዮጵያ ገንዘብን መደመር እና መቀነስ

**ትግበራ 9.1**

ከዚህ በታች በተሰጡት የብር ኖቶች ላይ በቡድን በመወያየት ድምራቸውን ጻፉ::

ሀ. 

ብር = _______ + ብር = _______ = ብር = _______

ለ. 

ብር = _______ + ብር = _______ = ብር = _______

# የኢትዮጵያ ዲናሮች ስም

| ተ.ቁ | የዲናሮች አይነት | የዲናሮች ምስል |
|---|---|---|
| 1. | ባለ አንድ ሳንቲም ዲናር |  |
| 2. | ባለ አምስት ሳንቲም ዲናር |  |
| 3. | ባለ አስር ሳንቲም ዲናር |  |
| 4. | ባለ ሃያ አምስት ሳንቲም ዲናር |  |
| 5. | ባለ ሃምሳ ሳንቲም ዲናር |  |
| 6. | ባለ መቶ ሳንቲም ዲናር (1ብር) |  |

## አስተውል/ይ

1ብር = 100ሳንቲም

1ብር = 20 ባለአምስት ሳንቲም ዲናር

1ብር = 10 ባለአስር ሳንቲም ዲናር

1ብር = 4 ባለሃያ አምስት ሳንቲም ዲናር

1ብር 1 = 2 ባለሃምሳ ሳንቲም ዲናር

## ምሳሌ 1

1 ባለ አምስት ሳንቲም ዲናር በስንት ባለ አንድ ሳንቲም ዲናሮች ይመነዘራል?

## መልስ

1 ባለ አምስት ሳንቲም ዲናር በ5 ባለ አንድ ሳንቲም ዲናሮች ይመነዘራል::

እንዴት? ለሚለው የሚከተለውን ምስል እይ/ዩ::

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
|  |  |  |  |  | |  |
| 1ሳ + | 1ሳ + | 1ሳ + | 1ሳ + | 1ሳ | = | 5ሳ |

## ምሳሌ 2

1 ባለሃያ አምስት ሳንቲም ዲናር በስንት ባለ አምስት ሳንቲም ዲናሮች ይመነዘራል?

## መልስ

1 ባለሃያ አምስት ሳንቲም ዲናር በ5 ባለአምስት ሳንቲም ዲናሮች ይመነዘራል::

እንዴት? ለሚለው የሚከተለውን ምስል እይ/ዩ::

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
|  |  |  |  |  | |  |
| 5ሳ + | 5ሳ + | 5ሳ + | 5ሳ + | 5ሳ | = | 25ሳ |

## ምሳሌ 3

1ባለ አንድ ብር ዲናር በስንት ባለ አስር ሳንቲም ዲናሮች ይመነዘራል?

## መልስ

1ባለ አንድ ብር ዲናር በ10 ባለ አስርሳንቲም ዲናሮች ይመነዘራል::

እንዴት? ለሚለው የሚከተለውን ምስል እይ/ዩ::

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
|  10ሳ |  10ሳ |  10ሳ |  10ሳ |  10ሳ |  |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
|  10ሳ |  10ሳ |  10ሳ |  10ሳ |  10ሳ | | |
| 20ሳ + | 20ሳ + | 20ሳ + | 20ሳ + | 20ሳ | = | 100ሳ ወይም 1ብር |

## ምሳሌ 4

1 ባለአንድ ብር ዲናር በስንት ባለሃምሳ ሳንቲም ዲናሮች ይመነዘራል?

## መልስ

ባለአንድ ብር ዲናር በ2 ባለሃምሳ ሳንቲም ዲናሮች ይመነዘራል::

እንዴት? ለሚለው የሚከተለውን ምስል እይ/ዪ::

| | | | |
|---|---|---|---|
|  |  | |  |
| 50ሳ + | 50ሳ | = | 100ሳ ወይም 1ብር |

# የኢትዮጵያ ብር ኖቶች

| ተ.ቁ | የ ብር ኖቱ አይነት | የ ብር ኖቱ ምስል |
|---|---|---|
| 1 | ባለ አምስት ብር ኖት |  |
| 2 | ባለ አስር ብር ኖት |  |
| 3 | ባለ ሃምሳ ብር ኖት |  |
| 4 | ባለ መቶ ብር ኖት |  |

| | | |
|---|---|---|
| 5 | ባለ ሁለት መቶ ብር ኖት |   |

## ምሳሌ 5

ሁለት ባለሃምሳ ብር ኖቶችን አንድ ላይ ብትደምር/ሪ ስንት ባለመቶ ኖት ብር ታገኛለህ/ሽ?

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
|   | |   | |  |
| 50 ብር | + | 50 ብር | = | 100 ብር |

## ምሳሌ 6

ከዚህ በታች የተሰጡትን የብር ኖቶች ደምር/ሪ:: ደምረህ/ሽ ስንት ብር አገኘህ/ሽ?

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
|   50 ብር | |   50 ብር   5 ብር | |  100 ብር   5 ብር |
| **50 ብር** | + | **55 ብር** | = | **105 ብር** |

## መልመጃ 9.1

1. ከዚህ በታች ያተሰጡትን የብር መጠን ደምር/ሪ::

   ሀ. 2ብር + 5ብር = _________ብር

   ለ. 40ብር + 55ብር = _________ብር

   ሐ. 19ብር + 62ብር = _________ብር

   መ. 43ብር + 37ብር = _________ብር

2. ከዚህ በታች የተሰጡትን የብር መጠን ቀናንስ/ሺ::

ሀ. 70ብር –30ብር = _________ብር

ለ. 100ብር–35ብር = ________ብር

ሐ. 65ብር – 31ብር = _________ብር

መ. 74ብር – 56ብር = _________ብር

ሠ. 85ሳንቲም – 72ሳንቲም = _________ ሳንቲም

3. አንድን ባለ ሁለት መቶ ብር ኖት

ሀ. ስንት ባለ አንድ መቶ ብር ኖት ይሆናል?

ለ. ስንት ባለ ሃምሳ ብር ኖት ይሆናል?

ሐ. ስንት ባለ አስር ብር ኖት ይሆናል?

መ. ስንት ባለ አምስት ብር ኖት ይሆናል?

4. ከዚህ በታች ለተሰጡትን ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ መልስ/ሺ::

ሀ. 1 ባለአምስት ብር ኖት ስንት ባለአንድ ብር ዲናር ይሆናል?

ለ. 1 አንድ ባለመቶ ብር ኖት ስንት ባለአስር ብር ኖት ይሆናል?

መ. 1 አንድ ባለሃምሳ ብር ኖት ስንት ባለአምስት ብር ኖት ይሆናል?

ሠ. 1 አንድ ባለመቶ ብር ኖት ስንት ባለሃምሳ ብር ኖት ይሆናል?

## 9.2 ግዢ እና ሽያጭ

### ትግበራ 9.2

ሀ. ቤተሰቦቻችሁ ከገበያ የሚገዙትን ነገሮች ከጓደኞቻችሁ ጋር ተነጋገሩበት::

ለ. ቤተሰቦቻችሁ በገበያ ላይ የሚሸጡትን ነገሮች ከጓደኞቻችሁ ጋር ተነጋገሩበት::

**ምሳሌ 7**

የአንድ ሳሙና ዋጋ 20 ብር ቢሆን የ4 ሳሙና ዋጋ ስንት ይሆናል?

## መፍትሔ

የ1ሳሙና ዋጋ = 20ብር

የ4 ሳሙና ዋጋ = ☐ብር

ስለዚህ የሳሙናው ዋጋ = 4 × 20 ብር = 80 ብር

## ምሳሌ 8

የአንድ ሲኒ ሻይ ዋጋ 5 ብር እና የአንድ ዳቦ ዋጋ 10 ብር ቢሆን በአጠቃላይ የሻዩ እና የዳቦው ዋጋ ስንት ይሆናል?

## መልስ

| | | |
|---|---|---|
|  |  |  |
| 5 ብር + | 10 ብር = | 15 ብር |

የአንድ ሲኒ ሻይ ዋጋ 5 ብር

የአንድ ዳቦ ዋጋ 10 ብር

በአጠቃላይ የሻዩ እና የዳቦው ዋጋ 10 ብር+ 5 ብር= 15 ብር ነው::

## ምሳሌ 9

ከዚህ በታች በተሰጡት ነገሮች ዋጋ ላይ በመመስረት የተሰጡትን ጥያቄዎች መልስ/ሺ::





















**ሀ.** ቶልቱ 15 ብር አላት:: ከላይ ዋጋቸው የተሰጡትን የተለያዩ ሶስት ነገሮችን መግዛት የምትችለው የትኞቹን ነው?

**መልስ፤** እርሳስ፣ ከረሜላ እና እርሳስ










**ለ.** ኢፋ 87 ብር አለው:: ኢፋ ምንም ብር ሳይቀርለት ከላይ ዋጋቸው የተሰጡትን የተለያዩ ሁለት ነገሮችን መግዛት የሚችለው የትኞቹን ነው?

**መልስ፤** መጽሐፍ እና ከረሜላ







**ሐ.** ገመቹስ 23 ብር አለው:: ገመቹስ ምንም ብር ሳይቀርለት ከላይ ዋጋቸው የተሰጡትን የተለያዩ ሁለት ነገሮችን መግዛት የሚችለው የትኞቹን ነው?

**መልስ፤** ደብተር እና ማስመሪያ







መ. ኤቢሴ 17 ብር አላት:: ኤቢሴ ምንም ብር ሳይቀርላት ከላይ ዋጋቸው የተሰጡትን የተለያዩ ሁለት ነገሮችን መግዛት የምትችለው የትኞቹን ነው?

መልስ፤ ብርቱካን እና ከረሜላ







### መልመጃ 9.2

1. የአንድ መጽሐፍ ዋጋ 160 ብር ነው:: መጽሐፉን ለመግዛት 200ብር ከሰጠህ/ሽ ስንት ብር ይመለስልሃል/ሻል?
2. የ1 ኪግ የስኳር ዋጋ 40ብር ከሆነ 2 ኪግ ስኳር ስንት ይሆናል?
3. ወረቀትን እንደ የኢትዮጵያ ዲናሮች እና ኖቶች በመስራት ክፍል ውስጥ ግዥ እና ሽያጭ አካሂዱ::

## 9.3 የቃላት ፕሮብሎሞችን ማስላት

### ትግበራ 9.3

መርጋ 5 ባለአስር ብር ኖት እና አንድ1 ባለሃምሳ ብር ኖት አለው:: መርጋ በአጠቃላይ ስንት ብር አለው?

## ምሳሌ 10

ጫልቱ አንድን በግ በ800ብር ሸጠች:: ጉዲና ደግሞ ሌላ በግ በ750ብር ሸጠ:: ጫልቱ የሸጠችበት ዋጋ ጉዲና ከሸጠበት በምን ያህል ይበልጣል?

## መፍትሔ

ጫልቱ የሸጠችበት ብልጫ 800 ብር - 750 ብር = 50ብር ይሆናል::

## ምሳሌ 11

ቶልቱ ዳቦ በ75ብር ገዝታ በ100 ብር ሸጠች:: የቶልቱ ትርፍ ምን ያህል ነው?

## መፍትሔ

ቶልቱ ዳቦ በ75ብር ገዛች:: በ100 ብር ሸጠች:: ትርፏ የሸጠችበት እና የገዛችበት ልዩነት ነው:: ስለዚህ 100ብር - 75ብር = 25ብር::

## መልመጃ 9.3

1. ቢሊሴ ከቤቷ 20 ብር ወስዳ ገበያ ሄደች::ገበያ ውስጥ እንቁላል በ30 ብር ሸጠች:: ቢሊሴ በአጠቃላይ ስንት ብር አላት?
2. ሲንቦ 1 ባለመቶ ብር ኖት እና 2 ባለሃምሳ ብር ኖት አላት:: ወቢ ደግሞ 3 ባለሃምሳ ብር ኖት 6 ባለአስር ብር ኖት አላት::ከሲንቦ እና ከወቢ ማን ብዙ ገንዘብ አለው?
3. ኢያና 3 ባለመቶ ብር ኖት እና 2 ባለሃምሳ ብር ኖት አለው::
   ሀ. ኢያና በአጠቃላይ ስንት ብር አለው?
   ለ. በ100 ብር መጽሐፍ ከገዛ ስንት ብር ይቀርለታል?
4. ለሚ 2 ባለመቶ ብር ኖት እና አንድ ባለ ሃምሳ ብር ኖት አለው:: ገመዴ ደግሞ 200 ብር አላት:: ገመዴ የብሯን ሩብ ለለሚ ሰጠችው::
   ሀ. ለሚ እና ገመዴ በአጠቃላይ ስንት ብር አላቸው?
   ለ. ለገመዴ ስንት ብር ይቀርላታል?
   ሐ. ለሚ በአጠቃላይ ስንት ብር አለው?

# ምዕራፍ 10




# የኢትዮጵያ የጊዜ አቀጣጠር

## 10.1 ጊዜን ከአናሎግ ሰዓት እና ከዲጂታል ሰዓት ላይ በሰዓት፣ በግማሽ ሰዓት እና በሩብ ሰዓት ማንበብ

**ትግበራ 10.1**

ተማሪዎች እስቲ የግርግዳ ሰዓቱን ምስል ተመልከቱ ፡፡

1. ደቂቃን የሚቆጥረው የትኛው ነው?
2. ሰዓትን የሚቆጥረው የትኛው ነው?
3. ረጅም ሆኖ በፍጥነት የሚዞረው የትኛው ነው?



የሚከተለው ምስል ሰዓት የሚቆጥር መሳሪያ ምስል ነው፡፡ መሳሪያውም ሰዓት ይባላል፡፡ እዚህ መሳሪያ ላይ ወፍራም አጭር እና ቀጭን ረጅም ቀስት ይታያል፡፡

ረጅሙ ቀስት ደቂቃን ያሳያል፡፡

አጭሩ ቀስት ሰዓትን ያሳያል፡፡

## ምሳሌ 1

በተሰጠው የሰዓት ምስል የሰዓቱ ቀስት 8ን ያመለክታል። የደቂቃው ቀስት ደግሞ ወደ 12 ያመለክታል። ይህም 8 ሰዓት መሆኑን ያሳያል። ሲነበብ ስምንት ሰዓት ተብሎ ይነበባል፡፡ ሲጻፍ 8:00 ይሆናል።

| | |
|---|---|
|  |  |
| **የአናሎግ ሰዓት** | **የዲጂታል ሰዓት** |

## አስተውል/ዪ

- የሰዓትም ሆነ የደቂቃ ቀስት ከግራ ወደ ቀኝ ነው የሚዞሩት።
- በአናሎግ ሰዓት ላይ በማናኛውም ሁለት ተከታታ ይቁጥሮች መካከል 5 ደቂቃ አለ።

## ምሳሌ 2

በሚከተለው ምስል ላይ ቀስቱ 3 ሰዓትን ያሳያል። ደቂቃው ደግሞ 12 ላይ ያመለክታል። ሲነበብ ሶስት ሰዓት ይሆናል። ሲጻፍ 3:00 ይሆናል።

| | |
|---|---|
|  |  |
| **የአናሎግ ሰዓት** | **የዲጂታል ሰዓት** |

## መልመጃ 10.1

1.የሚከተሉት የሰዓት ምስሎች ስንት ሰዓት እና ስንት ደቂቃ እንደሚያሳዩ ጻፍ/ፊ።

ሀ.


ለ.


ሐ.


መ.


2. ለተሰጡት የሰዓት ምስሎች ሰዓትን እና ደቂቃን የሚያሳዩ ቀስቶችን በመሳል አሳይ/ዪ።

ሀ.


5:30

ለ.


7:45

# 10.2 ሰዓት እና ደቂቃ

## ትግበራ 10.2

በ1 ሰዓት ውስጥ ስንት ደቂቃ አለ?

### አስተውል/ዪ

ሰዓት እና ደቂቃ የጊዜ መለኪያ ዩኒቶች ናቸው።

1 ሰዓት = 60 ደቂቃ

ግማሽ ሰዓት = 30 ደቂቃ

ሩብ ሰዓት = 15 ደቂቃ

## ምሳሌ 3

በሚከተለው የሰዓት ምስል ላይ በመመስረት የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች ሙለ/ዪ።

ሀ. አጭር እና ወፍራሙ ቀስት 12 ቁጥርን እና ቀጭን እና ረጅሙ ቀስት 6 ቁጥርን ካመለከተ ________ ሰዓት እና ________ደቂቃ ይሆናል።

ለ. አጭር እና ወፍራሙ ቀስት 1 ቁጥርን እና ቀጭን እና ረጅሙ ቀስት 3 ቁጥርን ካመለከተ ________ ሰዓት እና ________ደቂቃ ይሆናል።

ሐ. ቀጭኑ ረጅም ቀስት 9 ቁጥርን ካመለከተ ____ ደቂቃ ይሆናል።

መ. ቀጭኑ ረጅም ቀስት 4 ቁጥርን ካመለከ ____ ደቂቃ ይሆናል።




## መልስ

ሀ. አጭር እና ወፍራሙ ቀስት 12 ቁጥርን እና ቀጭን እና ረጅሙ ቀስት 6 ቁጥርን ካመለከተ 12 ሰዓት እና 30 ደቂቃ ይሆናል።

ለ. አጭር እና ወፍራሙ ቀስት 1 ቁጥርን እና ቀጭን እና ረጅሙ ቀስት 3 ቁጥርን ካመለከተ **1** ሰዓት እና 15 ደቂቃ ይሆናል።

ሐ. ቀጭኑ ረጅም ቀስት 9 ቁጥርን ካመለከተ 45 ደቂቃ ይሆናል።

መ. ቀጭኑ ረጅም ቀስት 4 ቁጥርን ካመለከ **20** ደቂቃ ይሆናል።

## መልመጃ 10.2

1. ከዚህ በታች ያሉትን ባዶ ቦታ ሙላ/ዪ።
   ሀ. 1 ሰዓት = ___________ ደቂቃ ነው።
   ለ. ግማሽ ሰዓት = _____________ ደቂቃ ነው።
   ሐ. ሩብ ሰዓት = ____________ደቂቃ ነው።
2. ከዚህ በታች ያሉትን ባዶ ቦታ ሙላ/ዪ።
   ሀ. 60 ደቂቃ = _______ ሰዓት ነው።
   ለ. 30 ደቂቃ = _______ ሰዓት ነው፡፡
   ሐ. 15 ደቂቃ = _______ ሰዓት ነው፡፡

# 10.3 የጊዜ የቃላት ፕሮብሌሞችን ማስላት

### ምሳሌ 4

አንድ መጽሀፍት ቤት በቅዳሜ ቀን ለአራት ሰዓት አገልግሎት ይሰጣል። መጽሀፍት ቤቱ ሶስት ሰዓት ላይ ቢከፈት ስንት ሰዓት ላይ ይዘጋል?

**መፍትሔ**

የሚከፈተው በ3 ሰዓት ላይ
ለአራት ሰዓት ተከፍቶ ይቆያል።
መጽሀፍት ቤቱ የሚዘጋበት ሰዓት 3:00 + 4:00 = 7:00 ይሆናል።

### ምሳሌ 5

ጂፋሬ ሁል ጊዜ ምሳ ከተመገበች በኋላ ለሩብ ሰዓት ታርፋለች። ጂፋሬ ለስንት ደቂቃ አረፈች።

**መፍትሔ**

ጂፋሬ ለሩብ ሰዓት እረፍት አረፈች። ስለዚህ ለ15 ደቂቃ እረፍት አረፈች።

## መልመጃ 10.3

1. ኢብሳ ከቤቱ እስከ ትምህርት ቤቱ ለመድረስ 30 ደቂቃ ይወስድበታል። ኢብሳ ስንት ሰዓት ወሰደበት ?
2. የትምህርት ክፍለ ጊዜ 2 ሰዓት ላይ ይጀመራል። የመጀመሪያው ደውል

30 ደቂቃ ቀድሞ ይደወላል። የመጀመሪያው ደውል ስንት ሰዓት ላይ ይደወላል?

3. ለቱ በ8 ሰዓት መጽሀፍት ቤት ገባች። ለ2 ሰዓት ካጠናች በኋላ ለሩብ ሰዓት በእግሯ በመጓዝ ወደ ቤቷ ተመለሰች። ስንት ሰዓት ላይ ቤቷ ተመለሰች?